# የአዲስ ኪዳን አምልኮ

J.C.Choate

World Literature Publications
Winona, Mississippi

© Copyright, World Evangelism Publications

This printing - 5,000 copies - 2023 – **Amharic**

**InDesign Layout**: Shane Fisher

**Translated by**: Belay Kebede Areri
**WhatsApp number**: 0913611000.
**Email**: ddcoc321@yahoo.co.uk

**Websites**:
www.worldevangelismlibrary.org
www.gospelgazette.com
www.worldevangelism.org
www.worldevangelismmedia.com

ማሳሰቢያ ፦ ለተማሪዎች መመሪያ ይህ መጽሐፍ አይሸጥም። መልሱን በራሳችሁ ወረቀት ላይ በመሥራት የመልስ መስጫ ወረቀታችሁንና መጽሃፉን ከዚህ በታች ባለው አድራሻ ላኩልን። ለበላይ ከበደ መልዕክት ሣጥን ቁጥር 1376 ድሬ ዳዋ ኢትዮጵያ፣ ስልክ 0913611000። ኢሜይል ddcoc321@yahoo.co.uk

**Printed by**:
World Evangelism Publications
Winona, MS 38967

# ማውጫ


ትምህርት አንድ__የአምልኮ ምንነት................................4
ትምህርት ሁለት_ አምላኪ...........................................7
ትምህርት ሦስት__የአምልኳቸን ግብ...........................11
ትምህርት አራት__የአምልኮ ዓይነት............................15
ትምህርት አምስት_የጥንቶቹ ክርስቲያኖች አምልኮ............18
ትምህርት ስድስት__የአምልኮ ቀን..............................22
ትምህርት ሰባት___የአምልኮ ሥርዓት..........................25
ትምህርት ስምንት__የመጽሃፍ ቅዱስ ጥናት...................29
ትምህርት ዘጠኝ___ፀሎት........................................33
ትምህርት አሥር___መዘመር.....................................37
ትምህርት አሥራ አንድ___የጌታ እራት መውሰድ...............41
ትምህርት አሥራ ሁለት__ስጦታ................................45
ትምህርት አሥራ ሦስት__በጉባኤ ላይ መገኘት.................48

## ትምህርት አንድ
## የአምልኮ ምንነት

አምልኮ የሚለው ቃል በመጽሃፍ ቅዱስ ውስጥ ማገልገል፤ማመስገን፤ ማክበር፤ ማወደስ ማለት ነው፡፡ ትርጉም ያለው እንዲሆን አስተዋይ ዋና ለሆነው ለሌላው ለሚመለከው መሰጠት ማለት ነው፡፡ እስቲ ትንሽ ጠለቅ ብለን እንመርምር

1 በማገልገል እናመልካለን

በዚህ ጉዳይ ላይ አገልጋይ የሚለው ቃል የሚያገለግል መታዘዝ ማምለክ ወዘተ ማለት ነው፡፡ ጳውሎስ ራሱን እንደአገልጋይ ደጋግሞ ገልፆአል፡፡ እንዲህ ይላል “ሃዋርያ ሊሆን የተጠራ የኢየሱስ ክርስቶስ ባሪያ ጳውሎስ በነቢያት ሁሉ አፍ በቅዱሳን መጽሃፍት አስቀድሞ ተስፋ ለሰጠው ለእግዚአብሄር ወንጌል ተለየ” (ሮሜ 1፡1) ጴጥሮስና ያዕቆብም በተመሳሳይ በ2ኛ ጴጥሮስ 1፡1 እና በያዕቆብ 1፡1 እንደሱ ብለዋል፡፡ ይህን ሲሉ ምን ማለታቸው ነው? እነሱ የሚሉት አሁንጌታን እያገለገሉ ህይወታቸውን ማንነታቸውን ሁሉ ነገራቸውን ለሱ መስጠታቸውን  ነው የሚናገሩጥ እኛም በተመሳሳይ እንደነሱ ማድረግ አለብን፡፡ ጳውሎስ ሲመክር “አሁን ግን ከኃጥያት አርነት ወጣቹሁ ለእግዚአብሄር ተገዝታቸው ልትቀደሱ ፍሬ አላቸው” ይላል (ሮሜ 6፡22)

ጌታ ምን ዓይነት አምልኮ ወይም ስግደት ከእኛ እንደሚፈልግ ለማየት የሚከተለውን ጥቅስ እናስትውል “ወደ እሲያ ከገባሁበት ከመጀመሪያ ቀን ጀምሮ በይህትና ሁሉና በእንባ ከአይሁድም ሴራ በደረሰብኝ ፈተና ለጌታ እየተገዛሁ ዘመኑን ሁሉ ከናንተ ጋር እንደኖርሁ እናንተም ታውቃላቹሁ” (ሓዋርያት 20፡19) “እንግዲህ በእናንተ ያለው መልካም ነገር አይሰደብ፡፡ የእግዚአብሄር መንግስት ፅድቅና ሠላም በመንፈስ ቅዱስም የሆነ ደስታ ናት እንጂ መብልና መጠጥ አይደለችምና እንደዚህ አድርጎ ለክርስቶስ የሚገዛ እግዚአብሄርን ደስ ያሰኛልና፡፡ በሰውም ዘንድ የተመሰገነ ነው፡፡ እንጊዲያስ  በሰላም የሚቆምበትን እርስበርሳችንም የምንታመንበትን እንከተል” (ሮሜ 14፡16.9)፤ “በመንፈስ የምትቃጠሉ ሁኑ ለጌታ ተገዙ” (ሮሜ 12፡11)

ስለአገልግሎታችን አስመልክቶ ጳውሎስ ሲፅፍ “እንግዲህ ወንድሞቸ ሆይ ሰውነታቹሁን እግዚአብሄርን ደስ የሚያሰኝና ሕያው ቅዱስም መስዋዕት አድርጋቹሁ ታቀርቡ ዘንድ በእግዚአብሄር ርህራሄ እለምናቸዋለሁ እርሱም ለአዕምሮ የሚመቸ አገልግሎታቹሁ ነው” (ሮሜ 12፡1) “ለስው ሳይሆን ለጌታ እንደምትገዙ በትጋትና በብጎ ፈቃድ ተገዙ”(ኤፌሶን 6፡7)  ጌታ ለትያጥሮን ቤተክርስቲያን እንዲ አላት “ሥራህንና ፍቅርህን እምነትህንም  አገልግሎትህንም ትዕግስትህንም ከፊተኛው ይልቅ የኋለኛው እንዲበዛ አውቃለሁ” (ዮሃንስ ራዕይ 2፡19)

በማገልገል ማምለክን ብዙ ጊዜ አውርተናል፡፡ ይህ ለጌታ የምናደርገው

በዚህ መልኩ ትክክል ነው። በሌላ አባባል ሙሉ ህይወታችንን ጊዜያችንን ለእግዚአብሄር ማዋል አለብን በዝህ መንገድ እሱን በማምለክ እንኖራለን ማለት ነው። እሱን የማናገለግል ከሆነ እንዴት አድርገን እሁድ ልናመልከው በህይወታችን ሁሉ ልናመልከው እንችላለን?

2 በማመስገን እናመልካለን

ሲላስና ጳውሎስ እስር ቤት በነበሩበት ጊዜ ተጽፎ የምናነበው “በመንፈቀ ሌሊት ግን ጳውሎስና ሲላስ እየፀለዩ እግዚአብሄርን በዜማ ያመሰኙ ነበር “ (የሃዋርያት ሥራ 16፡25) ጌታ እንዴት እንደባረከን ጳውሎስ ሲገልጽልን “ይሄውም በክርስቶስ አስቀድመን ተስፋ ያደርግን እኛ ለክብሩ ምስጋና እንሆን ዘንድ ነው” (ኤፌሶን 1፡12) ደግመን የምናነበው “እንግዲህ ዘወትር ለእግዚአብሄር የምስጋና መስዋዕት ማለት ለስሙ የሚመሰክሩ የከንፈሮችን ፍሬ ለእርሱ እናቅርብለት” (ዕብራዊያን 13፡15) ጴጥሮስም ሲነግረን “ነገር ግን በእሳት ምንም ቢፈተን ከሚጠፋው ወርቅ ይልቅ አብልጦ የሚከብር የተፈተነ እምነታችሁ ኢየሱስ ክርስቶስ ሲገለጥ ለምስጋናና ክብር ለውዳሴም ይገኝ ዘንድ አሁን ለጥቂት ጊዜ ቢያስፈልግ በልዩ ልዩ ፈተና አዝናችዋል.።” (1 ኛ ጴጥሮስ 1፡7) “ማንም የሚናገር ቢሆን እንደ እግዚአብሄር ቃል ይናገር የሚያገለግልም ቢሆን እግዚአብሄር በሚሰጠኝ ኃይል ነው ብሎ ያገልግል ክብርና ሥልጣን እስከ ዘላለም ድረስ ለርሱ በሚሆነው በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል እግዚአብሄር በነገር ሁሉ ይከብር ዘንድ አሜን” (1ኛ ጴጥሮስ 4፡11)

በማንኛውም ዕለታዊ ድርጊታችን ኑሯችን ንግግራችን በተለይ ደግሞ ጌታን ልናመልክ ብጌታ ቀን በምንሰበሰብበት ጊዜ ሁሌም ጌታን ልናመሰኘው ይገባል። ለአምልኮ በመገኘታችን ማመስገን አለብን በትክክለኛው ስሜት ውስጥ በመሆናችን ልናመሰነው ይገባናል። ልንሰግድለት በመቻላችን ልናመሰነው ይገባናል። ቃልን በማጥናታችን ለመፀለይ በመቻላችን ለመዘመር የጌታ እራት ለመውሰድ በስጦታ ሁሉ ለማምለክ በመቻላችን ልናመሰነው ይገባናል። እነዚህን ምስጋናዎች ካላቀረብን እንዴት ልናከብረው እንችላለን?

3 ለጌታ ክብር በመስጠት እናመልካለን

ክርስቶስ ሲናገር “ሰዎች ሁሉ አብን እንደሚያከብሩት ወልድን ያከብሩት ዘንድ ፍርድን ሁሉ ለወልድ ሰጠው እንጂ አብ በአንድ ሰው እንኳ አይፈርድም” (ዮሃንስ 5፡23) ጳውሎስም ሲፅፍ “ብቻውን አምላክ ለሚሆን ለማይጠፋው ለማይታየውም ለዘመናት ንጉስ ምስጋናና ክብር እስከ ዘላለም ድረስ ይሁን አሜን” (1ኛ ጢሞቴዎስ 1፡17)። ያዳነን ጌታ ነው። የባረከን እሱ ነው። የተሻለውን የህይወት ተስፋ የሰጠን እሱ ነው እናም ክብራችንንም ሊወስድ የሚገባው እሱ ነው።

4 ጌታን በማወደስ እናመልካለን

ማወደስ ማለት ከፍ ከፍ ማድረግ ማመስገን ማክበር ማለት ነው። ይህ የአምልኮን ትርጉም በመስጠት ከረዕሳቸን ጋር የሚስማማ ነው። እስቲ እንደገና ይህንን ሃሳብ የሚደግፍልንን እንመልከት "በአንድ ልብ ሆናችሁ በአንድ አፍ እግዚአብሄርን እርሱም የጌታቸን የኢየሱስ ክርስቶስ አባት ታከብሩ ዘንድ የትዕግስትና የመጽናናት አምላክ እንደክርስቶስ ኢየሱስ ፈቃድ እርስበርሳችሁ በአንድ ሃሳብ መሆንን ይስጣችሁ" (ሮሜ 15፥ 6) "በዋጋ ተገዝታቸዋልና ለራሳችሁ አይደላችሁም ስለዚህ በሥጋችሁ እግዚአብሄርን አክብሩ" (1 ኛ ቆሮንቶስ 6፡20) "ክርስቲያን እንደሚሆን ግን መከራን ቢቀበል ስለዝህ ስም እግዚአብሄርን ያመስኝ (1 ኛ ጴጥሮስ 4፡16)

በህይወት ዘመናችን የምንፈልገው የእኛን ሳይሆን የእግዚአብሄርን ስም ከፍ ከፍ ማድረግ ማክበር እሱን ብቻ ማመስገን ክብሩን ለርሱ ብቻ መስጠት ነው። ከርሱ ጋር ስናወዳድር እኛ ምንም ነገር አይደለንም። በጌታ ቀን ስንሰባሰብ ትኩረታቸን ሁሉ በእሱ ላይ አድርገን ልናመልከው ይገባል።

5 ጌታን ዝቅ ብለን በፍርሃት እናመልካለን

እግዚአብሄር ፈጣሪያቸን ነው። ክርስቶስ አዳኛቸን ነው።ልናከብራቸው ይገባል። ልንሰማቸው ይገባል። ልንታዘዛቸው ይገባል። በፊታቸው ዝቅ ልንል ይገባል፣ መዝሙረኛው ከብዙ ዓመታት በፊት እንዲ አለ "ስሙ የተቀደሰና የተፈራ ነው" አለ (መዝሙር 11፡9) የዕብራዊያን ፀሓፊም "ስለዚህ የማይናወጥ መንግስት ስለምንቀበል በማከበርና በፍርሃት እግዚአብሄርን ደስ እያሰኘን የምናመልክበትን ፀጋ እንያዝ" (ዕብራዊያን 12፡28)

ይህን የምናደርገው ጊታን ስንወድ በፊቱ ዝቅ ብለን ስንታዘዝ ከምስጋና ጋር ወደ እሱ ስንመጣ ያኔ በትክክል በፊቱ ልባቸንን የምናፈሰው ነፍሳቸንን ሁሉ ሰጠን ጌታን የምናመልከው የምናመሰግነው ስንሆን ነው። የዝህን ጊዜ በትክክል ጳውሎስ ያለውን የምናደንቅ ይሆናል "እግዚአብሄር አብን በእርሱ እያመሰገናቸው በቃል ቢሆን ወይም በሥራ የምታደርጉትን ሁሉ በጌታ ኢየሱስ ስም አድርጉት" (ቆላስያስ 3፡17)።

ብዙዎቸ ወደ አምልኮ የሚሄዱት ልምድ ስለሆነ ብቻ ወይም የሆነ ሰው ስለሄደ ብቻ የሚሄዱ አሉ። የተለመደ ስልሆነ ይሄዳሉ በርግጥ አያመልኩም። እነዝህ ሰዎቸ ስለአምልኮ ምንነት ያልመረመሩ እና ከአምልኳቸውም ምንም የማያገኙ ናቸው።

ለወደፊቱ ግን ስናመልክ በጠንካራ ፊላጎት እና አክብሮት መሆን አለብን። በንፁህ ልባቸን ከልብ ምስጋና ልንሰጥ ከፍ ከፍ ልናደርገው ልናከብረው ለምንጊዜውም ልንገዛው እና ጌታን የማምለክ ትርጉሙን ስንማር ስናውቅ ለእኛም ትርጉም ያለው ይሆናል ጌታም በትክክል ይመለካል።

## ጥያቄዎቸ

1. የትምህርቱን ርዕስ ጥቀስ

2. አምልኮ ምን እንደሆነ አብራራ
3. ትርጉም ያለው እንዲሆን እንዴት መደረግ አለበት?
4. ማገልገል የሚለው ቃል ምን ማለት ነው?
5. የእግዚአብሄር ልጅ እንዴት ባሪያ ይሆናል?
6. ጳውሎስ፤ ጴጥሮስ እና ያዕቆብ ባሪያዎች ነበሩ?
7. ጌታ ምን ዓይነት አምልኮ ይፈልጋል?
8. በዚህ ላይ የተወሰኑ ጥቅስኘችን ስጥ
9. ለምንድነው ለማምለክ ማገልገል የሚለውን ደጋግመን የምንናገረው?
10. ጌታን ሳንታዘዝ ልናመልከው እንችላለን?
11. ጌታን ማመስገን የሚለውን በሚያስተምረው ጥቅስ ላይ ተወያይ
12. ጌታን እንዴት ነው የምናመልከው?
13. ልጁን ሳናከብር አብን ማክበር እንችላለን?
14. ጌታ ለምንድነው የሚከበረው?
15. ክብር መስጠት ምን ማለት እንደሆነ ተናገር
16. በህይወት ዘመናችን ምን ማድረግ አለብን?
17. ብጌታ ቀን ለማምለክ የምንሰበሰብበት ዓላማ ምን እንድሆነ አብራራ
18. ፈጣሪያችን ማን ነው? አዳኛችንስ ማን ነው?
19. እንዴት አድርገን ነው ለነሱ ምላሽ የምንሰጠው?
20. ሊፈራ የሚገባው ስም ማን ነው?
21. ቆላስያስ 3፡17ን ጥቀስ
22. አብዛኛው ሰው እንዴት ነው የሚያመልኩት?
23. ለአምልኮ መቅረብ ያለብን በምን መንገድ ነው?

## ትምህርት ሁለት
## አምላኪ

ከእግዚአብሄር ፍጥረት ሁሉ እርሱን የሚያመልክ አንድ አለ እሱም የሰው ልጅ ነው፡፡እግዚአብሄር ሰውን የፈጠረው በአካል ብቻ ሳይሆን በነፍስና በ አዕምሮም በዕውቀትም ነው፡፡ከዚያም ሰው የመወሰን ችሎታ የማሰብ ችሎታም አለውስለዚህ ሰው እግዚአብሄርን ለማምለክ ሲመርጥ በእውነት የተመሰገነና የተከበረ ነው፡፡

ሰው በመሰረቱ አምላኪ ፍጡር ነው፡፡ አንድን ነገር ወይም አንድን ሰው ያመልካል፡፡ ሰው ሁልጊዜ አወቀም አላወቀም ይህንን ያደርጋል፡፡ የሆነ ነገር ያመልካል፡፡ ድሮም ሆነ አሁን ሰው ለሚያስበው ለሚፈራው ነገር ይንበረከካል፡፡ ያመልካል፡፡ ይህም ጨረቃን ክዋክብትን ድንጋዮችን ወንዞችን እና ማንኛውንም ዓይነት ተፈጥሮን ያጠቃልላል፡፡ ደግሞ ከድንጋይ ከእንጨት ከብረት ለተሠሩ ሰው ሰራሽ ምስሎች ሰግዷል

እየሰገዱም ነው። ነገር ግን ሰው መስገድ ካለበት ሊሰገድለት ለሚገባው ለፈጠረው ወደ ፈጠረው አምላክ ሊያመለክትና እንዲሰግድለት ሊበረታታ ይገበዋል። አምላክ እሱን እንዲያመልኩት እነዚህን ይፈልጋልና።

ኢየሱስ ሲያስተምር “ነገር ግን በእውነት የሚሰግዱ ለአብ በመንፈስና በእውነት የሚሰግዱበት ጊዜ ይመጣል አሁንም ሆኗል። አብ ሊሰግዱለት እንደነዚህ ያሉትን ይሻልና። እግዚአብሄር መንፈስ ነው። የሚሰግዱለትም በመንፈስና በእዉነት ሊሰግዱለት ያስፈልጋቸዋል” (ዮሃንስ 4፡23~24) ስለዚህ ለሰዎች መስገዳቸው ብቻ በቂ አይደለም ነገር ግን የሚሰግዱ ከሆነ በትክክለኛው መሰገድ ለሚገባው ሊሰግዱ ይገባቸዋል። ያም ስግደት ሊፈጸም የሚገባው በመንፈስና በውነት መሆን አለበት ። እስቲ ይህ ምን ለመግለፅ እንድሆነ እንመልከት

1. ሁሉም ስለእውነተኛው እና ህያው አምላክ ሊያውቁ ይገባል። ሁሉም ፍጥረት ወደ ሰሪው ይጠቁማል። ይህ የማይታለፍ እና ሁሉም የማሰብ ችሎታ ያላቸው የሰው ልጆች ሁሉ የጉዳይን እውነታዎች ሲቀበሉ እዚህ መደምደሚያ ላይ ለመድረስ ይገደዳል በርግጥ እውነተኛና ህያው እግዚአብሄር ፈጣሪ እንደሆነ እናውቃለን (ዘፍጥረት 1፡1)።

2. እግዚአብሄር የሁሉም ነገር ፈጣሪ ከሆነ የሰው ልጅ ሊታዘዘው ይገባል። ሰውን እንዲታዘዝ ደግሞ እግዚአብሄር ምን ማድረግ እንደሚገባቸው ፈቃዱን ይገልጥላቸዋል። ይህንን ደግሞ አድርጎታል። ይህንንም ፈቃዱን በመጽሃፍ ቅዱስ ውስጥ ገልጧል። የተነገረንም ስለክርስቶስ የተነገረን ያነበብነው በሱ እንድናምንና ይህ እምነታችን ህይወት እንዲሆነን ነው (ዮሃንስ 20፡30~31) ከዚህም በላይ መጽሃፍ ቅዱስ በእግዚአብሄር መንፈስ የተሰጠ መሆኑ ነው (2 ጢሞቴዎስ 3፡ 1~17)

3. እግዚአብሄር ከተናገረ እና የተናገረው ደግሞ በመጽሃፍ ቅዱስ ገጾች ተመዝግቦ ካለ ለሰው ልጆች ወደ መጽሃፍ ቅዱስ መጥተው ለመገናኘት ይችላሉ። ሊማሩት ሊያጠኑት ይችላሉ። ክርስቶስ ለሓዋርያቶች ወደ ዓለም ሁሉ ሄደው ወንጌልን ለፍጥረት ሁሉ እንዲሰብኩ አዟቸዋል (ማርቆስ 16፡15~16) ይህ ብቻ አይደለም ፅድቅን የሚራቡና የሚጠሙ ይጠግባሉ ብሏል (ማቴዎስ 5፡6) ይህ ብቻ አይደለም ጌታን ማወቅ የሚፈልጉ እና የሚቀበሉትን ለእነሱ የእግዚአብሄር ልጅ የመሆን መብትን ሰጧቸዋል። (ዮሃንስ 1፡12)

4. አንድ ጊዜ የእግዚአብሄርን ቃል ማንበብና ማጥናት ከቻለ በልቡ ውስጥ እምነት ይፈጠራል (ሮሜ 10፡17) በእውቀትና በእምነት የጌታን ት ዕዛዝ ወደ መታዘዝ በመምጣትና ደህንነቱን ሊያገኝ ይችላል (ሓዋርያት 2፡ 38፤ ሃዋርያት ሥራ 17፡30፤ ዕብራዊያን 11፡6)

5. በመታዘዝ ይድናል ከዚያ አሁን ክርስቲያን ሆኖ ወደ ጌታ ቤተክርስቲያን ይጨመራል (ሃዋርያት ሥራ 2፡47፤ ሃዋሪያት ሥራ 11፡26)።

6. እንደቤተክርስቲያን አባልና እንደ ክርስቲያን ጌታን ለማምለክ በትክክለኛው መንገድ ለእርሱ መስገድ ይችላል። ይህንን ከማድረጉ በፊት ማንም ሰው በትክክለኛው መንገድ በመጽሃፍ ቅዱሳዊ መሰረት እየሰገደ አልነበረም። ይህንን እናንብብ "እግዚአብሄርን የሚፈራ ፈቃዱንም የሚያደርግ ቢኖር ያንን እግዚአብሄር ይሰመዋል እንጂ ኃጥያተኞችን እንዳይሰማ እናውቃለን (ዮሃንስ 9፡31) አንድ ሰው በእግዚአብሄር ለመሰማት ሁለት ሁኔታዎች መኖር አለባቸው። የመጀመሪያው የእግዚአብሄር አምላኪ መሆን አለበጥ ሁለተኛው በርግጥ እርሱ የጌታን ቃል አድራጊ በመሆን ላይ የተመሰረተ ነው። ይህ ማለት ከእግዚአብሄር ጋር ትክክለኛ ግንኙነት ወይም የወልድ እና የአብ ግንኙነት ወይም ክርስቲያንና የጌታ ቤተክርስቲያን አባል መሆን አለበጥ

7. እንደ ክርስቲያንና እንደክርስቶስ ቤተክርስቲያን አባል በአምልኮ ጊዜ አስፈላጊ የሆኑ ነገሮች ጌታን በመንፈስ እና በእውነት ማምለክ አለበጥ ይህ አምልኮ በእግዚአብሄር ዘንድ ተቀባይነት ያለው ነው። ያም ማለት አምልኮው በትክክለኛ የአዕምሮ ማዕቀፍ ውስጥ መቅረፅ አለበት ማለት ነው። ይሄው ነው። ከልብ በትህትና በቅንነት እና በአክብሮት መደረግ አለበጥ እንዲህ ያለው የልብ ንፅህና በሚሠራው ነገር ላይ ማተኮርን ይጠይቃል። ከዚያም በመጨረሻም አምልኮው በሁሉም እውነት ላይ መሳተፍ አለበጥ ይህ ማለት ከእግዚአብሄር ቃል ትምህርት ጋር የሚስማማ መሆን አለበት ማለት ነው። አሁን ጥያቄው ጌታ ያስተማረው ምንድነው? የሚለው ነው ጥናታችንን ስንቀጥል ይህ የመጽሃፍ ቅዱስ ጥናትን፣ ፀሎትን፣መዝሙርን፣የጌታ እራትን፣ ስጦታን እንደሚጨምር እንረዳለን። ከዚህም በላይ ጌታ በወሰነው የጌታ ቀን እንዲሆን እጠይቃል። አሁን አንድ ለዚህ የጌታ ትምህርት ቅን ሲሆን ሲታዘዝ ለውጥ ያመጣል። አምልኮው እንደእውነቱ ካልሆነ በቀር ሁሊም ከንቱ ነው። በተጨማሪም አንድ ሰው የጌታን ትምህርት ወደ አምልኮ ቢከተልም አምልኮው በመንፈስ ካልሆነ ወይም በማስተውል ካልሆነ ከንቱ ነው። እግዚአብሄር ሰዎች እንዴት ሊያመልኩት እንደሚገባቸው ገልፆአል። ሰውም ያንን ሊታዘዝ ይገበዋል።

8. አምላኪ ሰው በትክክለኛ ቦታ ላይ ተገኝቶ ማምለክ አለበት ። ያም ትክክለኛ ቦታ የክርስቶስ ቤተክርስቲያን ነው። በትክክለኛው አምልኮ ጋር ሲስማማ እዚያ ቦታ ጌታ ይገኛል። እናም ከትክክለኛ አምላኪ ሰዎች ጋር መሆንም ነው በዚህን ጊዜ አምልኮው ተቀባይነት ይኖረዋል።

ህብረት በጣም አስፈላጊ ነው። እውነተኛ ክርስቲያን ከተለያዩ የሃይማኖት ድርጅቶች ጋር ማምለክ አይችልም። ወይም ከዬትኛውም የሃይማኖት ተቋም ጋር ማምለክ አይችልም ከክርስቶስ ቤተክርስቲያን ውጪ ማምለክ አይችልም። ምክንያቱም አምልኳቸው ከተፃፈው የጌታ ፈቃድ ከሆነው አምልኮ በጣም ይለያል። የጌታ ቤተክርስቲያን አባል ወይም እውነተኛ ክርስቲያን ከሣምንቱ 7ኛ ቀን ማምለክ አይችልም።

ሰው ሰራሽ ከሆነ እና በሰው ሃሳብና እምነት አኳያ ከሚያመልኩት ጋር ማምለክ አይቻልም። ለሁሉም ዓለም አብያተክርስቲያናት ከሚፀልዩ ጋራ ማምለክ አይቻልም በሙዚቃ መሳሪያ ከሚያመልኩ ጋር ማምለክ አይቻልም የጌታ እራትን በየሳምንቱ የመጀመሪያ ቀን ከማይወስዱ ጋር ማምለክ አይቻልም ። በክራት ወይም አስራትን ከሚሰብኩ እና ከሚሰበስቡ ጋር ማምለክ አይቻልም ጳውሎስ ሲናገር "ፍሬም ከሌላቸው ከጨለማው ሥራ ጋር አትተባበሩ ይልቁንም ግለጡት እንጂ" ይላል (ኤፌሶን 5፡11)፤ ዮሃንስም በመለዕክቱ እንዲህ ይላል "ሠላም የሚለው ሰው በክፉ ሥራው ይካፈላልና" ይላል (2 ዮሃንስ 11)።

9. አምላኪ እራሱ ምንም እንኳን አምላኪው ፍፁም ባይሆንም እንደወደደ የመኖር ፊቃድ አይሰጠውም። ጌታን ማምለክ ካለበት መጥፎ ልማዶቹን እና ልምምዶቹን ማስወገድ አለበት (ያዕቆብ 5፡17) እና በንፁህ ልብ በንፁህ አካል በትህትና መንፈስ ወደ ጌታ ለመቅረብ መጣር አለበት

አንተ ምን ዓይነት አምላኪ ነህ? መቼ ነው የምታመልከው? ምን ያህል ጊዜ ነው የምታመልከው? ለምን ታመልካለህ? ማንን ታመልካለህ? ብዙ አምላኪዎች አሉ ነገር ኚ ጥቂት እውነተኛ አምላኪዎች ናቸው ያሉጥ ብዙውቹ የተሳሳተ ነገር ያመልካሉ  ወይም ትክክለኛውን በተሳሳተ መንገድ ያመልካሉ አንተ የምታመልክ ከሆነ ትክክለኛውን አምላክ ወይም እውነተኛውን በትክክለኛ መንገድ እንድጸግድለትና  ጌታ ሊሰገድለት የሚፈልገው ዓይነት ሰው መሆንህን እርግተኛ ሁን

## ጥያቄዎች

1. ከእግዚአብሄር ፍጥረት ውስጥ ፈጣሪውን የሚያመልክ ፍጡር ማንነው?
2. እግዚአብሄር ሰውን እንዴት ፈጠረ?
3. የሰው ልጅ መወሰን የሚችለው ምንድነው?
4. መቼ ነው እግዚአብሄር በትክክል የሚከብረው?
5. የሰው ልጅ በመሰረቱ ምንድነው?
6. እስቲ የሰው ልጅ በህይወቱ የሚያመልካቸውን የተወሰኑ ጥቀስ
7. እግዚአብሄር እንዴት የሚያመልኩትን ይሻል?
8. ዮሃንስ 4፡23~24ን አንብብና አብራራ
9. ወደ እግዚአብሄር የሚያመለክተው ማን ነው?
10. ዘፍጥረት 1፡1 ጥቀስ
11. እግዚአብሄር ፈቃዱን ለሰዎች ገልፆአል?
12. ይህን እንዴት አድርጎ ነው የገለጠው?
13. ዮሃንስ 20፡30~31 እና 2 ጢሞቴዎስ 3፡16~17ን አንብብ
14. ሰዎች የሱን ፈቃድ እንዲያውቁ እግዚአብሄር ለምን ይፈልጋል?
15. የእግዚአብሄርን ፈቃድ ማወቅ ለሰው ልጅ ይቻላል?

16. ጌታ የእግዚአብሄር ልጅ እንዲሆን ኃይል ለማን ሰጠ?
17. እምነት በአንድ ሰው ልብ ውስጥ እንዴት የፈጠራል?
18. በምን መንገድ ነው ሰው የሚድነው?
19. ማን ነው ጌታን ለማምለክ የሚዘጋጀው?
20. እግዚአብሄር አጥያተኞችን ይሰማል?
21. የአንድ ሰው ከእግዚአብሄር ጋር ግንኙነት ምንድነው?
22. በመንፈስና በእውነት ማምለክ ማለት ምን ማለት ነው?
23. እያንዳንዱ የሚያመልክበት ዬት ነው?
24. ህብረት ለምን ያስፈልጋል?
25. እውነተኛ ክርስቲያን ሊለማመድ የማይገባውን ጥቀስ
26. አምላኪ ወደ ጌታ መቅረብ ያለበት እንዴት ነው?
27. እውነተኛ አምላኪዎቸ ብዙ አሉ?

## ትምህርት ሦስት
## የአምልኳችን ግብ

ከፍጥረት ጀምሮ ሰው ከፀሃይ በታቾ ያለውን ሁሉ ያመልክ ነበር። እንዲያውም ፀሃይ ራሱን ያመልክ ነበር። በዓለም ዙሪያ በሚሊዮን የሚቆጠሩ አማልክት እና አማልክቶቸ አሉ። ድንቅ ቤተመቅደስ በአምላኪዎቻቸው ተገንብተዋል። ነገር ግን አብዛኛዎቹ ሰዎቸ (አማኞቻቸው) ደስተኛ ያልሆኑ ይመስላሉ። ለምን? ምንድነው ስህተቱ?

ስህተቱ ብዙ ሰዎቸ በአንድ እና በእዉነትኛው ህያው አምላክ ማመን አለመቻላቸው ነው። ክርስቶስ ወደዚህ ህያው አምላክ ይጠቁማል ወይም ያመለክታል እንዲህ አለ "እግዚአብሄር መንፈስ ነው የሚሰግዱለትም በመንፈስና በእውነት ሊሰግዱለት ይገባቸዋል" (ዮሃንስ 4፡24) እንግዲህ እግዚአብሄር የሰው አምልኮ ግብ መሆን አለበጥ ይህንን ሲያውቅና አምልኮውን ወደ እግዚአብሄር ሲያመራ ብቻ ለረጂም ጊዜ ሲፈልገው የነበረውን የነፍስ ሠላም እና ምቾት ማግኘት ይቾላል።

በዚህ አጭር ትምህርት ውስጥ አምላክ ማን እንድሆነ እና ለምን እሱን ማምለክ እንዳለብን ለማወቅ እንሞክራለን

1. እግዚአብሄር የሁሉም ነገር ፈጣሪ ነው

"በመጀመሪያ እግዚአብሄር ሰማይንና ምድርን ፈጠረ" (ዘፍጥረት 1፡1) መጽሃፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል ብሎ ማለት ይቻላል ነገር ግን ሌላ ምን ማረጋገጫ አለ? ዝም ብለህ ዙሪያህን ተመልከት እና እግዚአብሄር የፈጠረውን ተመልከት ። ምድርና በውስጧ ያሉት ነገሮቸ ሁሉ ለአምላክ መኖር በቂ ማረጋገቻ ሆነው ያገለግላሉ። አንድ ነገር ከምንም ሊመጣ አይቾልም ስለዚህ አንድ የፈጠረው አካል አለ። ዳዊት እንዲህ ይላል "ሰማያት የእግዚአብሄርን ክብር ይናገራሉ፤ የሰማይም ጠፈር የእጁን ሥራ ያወራሉ" (መዝሙር 19፡1) በዚህ ማን ተከራከረ? ማንስ ሊከራከር

ይቻላል?

እግዚአብሄር ወንድና ሴትን በአምሳያው ፈጠረ፡፡ "እግዚአብሄርም አለ ሰውን በመልካቸን እንደምሳሌያችን እንፍጠር የባህር አሶችንና የሠማይ ወፎችን እንሣትንና ምድርን ሁሉ በምድር ላይ የሚንቀሳቀሱትንም ሁሉ ይግዙ፡፡ እግዚአብሄርም ሰውን በመልኩ ፈጠረ በእግዚአብሄር መልክ ፈጠራቸው፡፡ (ዘፍጥረት 1፡26~27) "እግዚአብሄር አምላክም ሰውን ከምድር አፈር አበጀው በአፍንጫውም የህይወት እስትንፋስን እፍ አለበት ሰውም ህያው ነፍስ ያለው ሆነ" (ዘፍጥረት 2፡7)

2. እግዚአብሄር ሰዎችን ከኃጥያታቸው ያድን ዘንድ ልጁን ኢየሱስን ላከ

የጌታን መምጣት በተመለከተ የምናነበው "እርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ህይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሄር አንዲያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዷልና፡፡ ዓለም በልጁ እንዲድን ነው እንጂ በዓለም እንዲፈርድ እግዚአብሄር ወደ ዓለም አልላከውም" (ዮሃንስ 3፡16~17)፡፡ ጳውሎስ ሲፅፍ "ነገር ግን ገና ኃጥያተኞች ሳለን ክርስቶስ ስለእኛ ሞቶአልና እግዚአብሄር ለእኛ ያለውን የራሱን ፍቅር ያስረዳል" (ሮሜ 5፡8) በመቀጠልም "ሰዎች ሁሉ ሊድኑና እውነቱን ወደ ማወቅ ሊደርሱ በሚወድ በእግዚአብሄር በመድኃኒታችን ፊት መልካምና ደስ የሚያሰኝ ይህ ነው" ( 1ኛ ጢሞቴዎስ 2፡3~4) ስለደህንነታችንም እንዲህ ብሎ ጽፏል "ይህም የእግዚአብሄር ስጦታ ነው እንጂ ከናንተ አይደለም፡፡ ማንም እንዳይመካ ከሥራ አይደለም" (ኤፌሶን 2፡8~9)

3. እግዚአብሄር በመንፈሳዊም በአካልም በሁሉ ነገር ባርኮናል ያዕቆብ ሲፅፍ እንዲህ ይላል "በጎ ስጦታ ሁሉ ፈፁምም በረከት ሁሉ ከላይ ናቸው፡፡መለወጥም በእርሱ ዘንድ ከሌለ ከብርሃናት አባት ይወርዳሉ" (ያዕቆብ 1፡17)፡፡ ጳውሎስ ሲናገር "ከክርስቶስ በሰማያዊ በረከት ሁሉ የባረከን የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና አባት ይባረክ" (ኤፌሶን 1፡3)

4. አንድ እውነተኛና ህያው አምላክ አለ

ስለ እግዚአብሄር አንድነት ሲናገር ጳውሎስ እንዲህ አለ "ከሁሉ በላይ የሚሆን በሁሉም የሚሠራ በሁሉም የሚኖር አንድ አምላክ አለ" ብሏል፡፡ (ኤፌሶን 4፡6) ቀጥሎም "አንድ እግዚአብሄር አለና በእግዚአብሄርና በስውም መካከል ያለው መካከለኛው ደግሞ አንድ አለ እርሱም ሰው የሆነ ክርስቶስ ኢየሱስ ነው ራሱንም ለሁሉ ቤዛ ሰጠ" (1 ኛ ጢሞጤዎስ 2፡5)

5. እግዚአብሄር መንፈስ ነው፡~ በዮሃንስ 4፡24 ላይ እግዚአብሄር መንፈስ እንደሆነ በግልፅ ተናግሯል በሌላ አነጋገር እግዚአብሄር ሥጋና ደም አይደለም፡፡ እሱ አካላዊ አይደለም፡፡ እርሱ ቁሳዊ አይደለም፡፡ ስለዚህም እርሱ መንፈስ መሆኑን ስንማር እርሱን እንደሰው ደረጃ ሳይሆን በሌላ መንፈሳዊ ዓለም ውስጥ እንዳለ እስከምንቀጥረው ድረስ በደንብ ልንረዳው እንችላለን፡፡

6. እግዚአብሄር ፍቅር ነው፦ ዮሃንስ ሲያውጅ “ፍቅር የሌለው እግዚአብሄርን አያውቅም። እግዚአብሄር ፍቅር ነውና። በዚህ የእግዚአብሄር ፍቅር በእኛ ዘንድ ተገለጠ በእርሱ በኩል ህይወት እንኖር ዘንድ እግዚአብሄር አንድ ልጁን ወደ ዓለም ልኮታልና ፍቅርም እንዲዚህ ነው። እግዚአብሄር እርሱ ራሱ እንደወደደን ስለአጥያታችንም ማስተሰርያ ይሆን ዘንድ ልጁን እንደላከ እንጂ እኛ እግዚአብሄርን እንደወደድነው አይደለም ወዳጆች ሆይ እግዚአብሄር እንዲ አድርጎ ከወደደን እኛ ደግሞ እርስበርሳችን ልንዋደድ ይገባናል” ( 1ኛ ዮሃንስ 4፡8~11) እያለ ያለው ምንም ፍቅር ከሌለን እግዚአብሄርን ልናውቀው አንችልም። ምክንያቱም እግዚአብሄር ራሱን የገለጠው በፍቅር ነውና።

7. እግዚአብሄር ህያው ነው

ጴጥሮስ ሲመሰክር “አንተ የህያው አምላክ የእግዚአብሔር ልጅ ነህ”(ማቴዎስ 16፡16) ጳውሎስ ከጣኦታት ተመልሰው ወደ ህያው አምላክ ዘወር ያሉትን ተናግሯቸዋል (1ኛ ተሰሎንቄ 1፡9) አንዳንዶች እግዚአብሔር እንደሞተ ያውጃሉ እነሱ በመንፈስ የሞቱ ናቸው። እግዚአብሔር አለ። ክርስቶስ ሲይስተምር “እግዚያብሔር የህያዋን አምላክ እንጂ የሙታን አምላክ አይደለም” (ማቴዎስ 22፡32)

8. ለእግዚአብሔር ሁሉ ይቻላል

ኢየሱስ ማን ሊድን እንደሚችል ለሰዎች ሲናገር እንዲህ አለ “ይህ በሰው ዘንድ አይቻልም በእግዚአብሔር ዘንድ ግን ሁሉ ይቻላል” አላቸው።(ማቴዎስ 19፡26)

9. ከእግዚአብሔር በቀር ቸር የለም

“ስለምን ቸር ትለኛለህ? ከአንዱ ከእግዚአብሔር በቀር ቸር ማንም የለም”(ማርቆስ 10፡18)

10. እግዚአብሄርን ማንም አላየውም

ዮሃንስ ሲፅፍ “መቼም ቢሆን እግዚአብሄርን ያየው የለም በአባቱ እቅፍ ያለ አንድ ልጁ ተረከው” (ዮሃንስ 1፡18)

በመቀጠልም አምላክ ለሰው ፊት የማያዳላ መሆኑን (የሓዋርያት ሥራ 10፡34~35) የሁሉንም ሥራ ከዓለም መጀመሪያ ጀምሮ እንደሚያውቅ (የሓዋሪያት ሥራ 15፡18) በመጨረሻም በኢየሱስ በሰው ዘንድ የተሰወረውን ሚስጥር እንደሚፈርድ ልንገነዘብ እንችላለን (ሮሜ 2፡16) የዘላለምን ህይወት እንዲሰጥ እናውቃለን ( 1ኛ ዮሃንስ 5፡11) ወዘተ።

ስለ እሱ የምናወራው እግዚአብሄር ሁሉን የሚያውቅ ሁሉን የሚያይ በአንድ ጊዜ ሁሉ ቦታ የሚገኝ ኃይለኛ እና መጀመሪያም መጨረሻም ስለሌለው አምላክ ነው ያወራነው። ከርሱ ጋር ሊወዳደር የሚችል ማንም የለም። እርሱ የሁሉ ነገር ፈጣሪ ነው። እሱ ብቻ ሊመለክ ሊሰገድለት ሊመሰገን ሊከብር ከፍ ከፍ ሊደረግ የሚገባው ነው። ይህም ደግሞ

የሚሆንለት አሁንም ለዘላለምም ነው።
አምላክ የእኛን አምልኮ ይፈልጋል ነገር ግን ለእርሱ ክብር እንድንሰጥ በፉፁም አያስገድድም። ነገር ግን ይህን ለማድረግ እሱን የመረጡት በዚህ መሰረት ይባረካል።
ይሁን እንጂ ማንኛውንም ዓይነት አምልኮ አይቀበልም ልንሰግድለት ከፈለግን በኛ ሳይሆን በእሱ ውል መሰረት መሆን አለበጥ የሚፈልገውን የአምልኮ ዓይነት በቃሉ ገልጦታል ይህንንም በሚቀጥለው ትምህርት እንመለከታለን

## ጥያቄዎች

1. የሰው ልጅ ምንን በማምለክ ይታወቃል?
2. አብዛኞቹ የሃማኖት ሰዎች ስህተት የሆነውን ግለፅ
3. ዮሃንስ 4፡24 ጥቀስ
4. የስው ልጆችህ የአምልኮ ግብ ምን መሆን አለበት?
5. ዘፍጥረት 1፡1 ተናገር
6. ስለእግዚአብሄር ህያውነት ማረጋገጫ ስጥ
7. የእግዚአብሄርን ክብር የሚያውጅ ምንድነው?
8. እግዚአብሄር ወንድና ሴትን እንዴት አድርጎ ፈጠረ?
9. እግዚአብሄር ልጁን ወደ ዓለም ለምን ላከ?
10. ዮሃንስ 3፡16~17 ጥቀስ
11. የሞተልን ማን ነው?
12. እንዴት ነው የዳንነው?
13. የእኛ በረከት በሙሉ የመጣው ከዬት ነው?
14. ኤፌሶን 1፡3 አንብብ
15. ጳውሎስ ስለእግዚአብሄር አንድነት ምን አለ?
16. እግዚአብሄርን እንዴት ትገልፃለህ?
17. “እግዚአብሄር ፍቅር ነው” የሚለውን አብራራ
18. እግዚአብሄር ዛሬም አለ? በምን መንገድ?
19. ለእግዚአብሄር ሁሉ ይቻለዋል?
20. ቸር ማን ነው?
21. እግዚአብሄርን ያየ ሰው አለ?
22. እግዚአብሄር ለሰው ያዷላል?
23. በዓለም የሚፈርዷው ማን ነው?
24. የእግዚአብሄርን ባህሪያት ጥቂት ግለፅ
25. እግዚአብሄር ምን ዓይነት አምልኮ ይፈልጋል?

## ትምህርት አራት
## የአምልኮ ዓይነቶች

በአዲስ ኪዳን ገፆች ውስጥ ስንሄድ ሦስት ዓይነት አምልኮዎች ተገልፀዋል። በዚህ ትምህርት ውስጥ እያንዳንዱን እንመለከታለን። ይህንን የምናደርገው በቅዱሳት መጻህፍት ውስጥ ከአንድ በላይ አምልኮ እንዳለ ለማስታወስ ነው። እናም በተመሳሳይ ጌታ ዬትኛውን እንድንሳተፍ እንደሚፈልግ ለማወቅ በነዚ በተለያዩ የአምልኮ ዓይነቶች ላይ ጥናት እናደርጋለን። እነዚህ በዙሪያችን ያሉ ብዙ ሰዎች አምላኪዎች ስለሆኑ ብቻ አምልኳቸው በእግዚአብሄር ዘንድ ተቀባይነት አለው ማለት አለመሆኑን ማመን አለብን

1. ቅዱሳት መጽሃፍት ስለ ባለማወቅ አምልኮ ይናገራል

“ጳውሎስም በአቴና ሲጠብቃቸው ሳለ በከተማው ጣኦት መሙላቱን እየተመለከተ መንፈሱ ተበሳጨበት። ስለዚህም በምኩራብ ከአይሁድና እግዚአብሄርን ከሚያመልኩ ሰዎች ጋር በየቀኑም በገበያ ከሚያገኛቸው ጋር ይነጋገር ነበር።ከኤፊቆሮስ ወገንና ኢስጣኢኮችም ከተባሉት ፈላስፎች አንዳንዶቹ ከእርሱ ጋር ተገናኙ አንዳንዶቹም ይሄ ለፍላፊ ምን ሊናገር ይወዳል? አሉ። ሌሎችም የኢየሱስንና የትንሳኤውን ወንጌል ስለሰበከላቸው አዲሶችን አማልክትን የሚያወራ ይመስላል አሉ። ይዘውም ይህ የምትናገረው አዲስ ትምህርት ምን እንደሆነ እናውቅ ዘንድ ይቻለናል? በጆሯችን እንግዳ ነገር ታሰማናለህ? እንግዲህ ይሄ ነገር ምን እንደሆነ እናውቅ ዘንድ እንፈቅዳለን ብለው አርዮስፋገስ ወደ ተባለው ሥፍራ ወሰዱት። የአቴና ሰውች ሁሉና በዚያ የኖሩ እንግዶች አዲስ ነገርን ከመናገር ከመስማት በቀር በሌላ ጉዳይ አይውሉም ነበር። ጵውሎስም በአርስፋጎስ መካከል ቆሞ እንድህ አለ “የአቴና ሰዎች ሆይ እናንተ በሁሉ ነገር አማልክትን እጅግ  እንደምትፈሩ እመለከታለሁ የምታመልኩትን እየተመለከትኩ ሳልፍ ለማይታወቅ አምላክ  የሚል ፅህፈት  ያለበትን መሰዊያ ደግሞ አግኝቸአለሁና። እንግዲህ ይህን ሳታውቁ ኡእምታመልኩትን እኔ እነግራቸዋለሁ። ዓለሙን እና በእርሱ ያለውን ሁሉ የፈጠረ አምላክ እርሱ ኡእሰማይና የምድር ጌታ ነውና እጅ በሰራው መቅደስ አይኖርም። እርሱም እስትንፋስን ሁሉንም ለሁሉ ይሰጣልና አንዳች እንደሚጎድለው በሰው እጅ አይገለገልም። ምናልባትም እየመረመሩ ያገኙት እንደሆነ እግዚአብሄርን የፈልጉ ዘንድ በምድር ሁሉ ላይ እንዲኖሩ የሰውን ወገኖች ሁሉ ከአንድ ፈጠረ የተወሰኑትንም ዘመኖች ለሚኖርበት ሥፍራ ዳርቻ መደበላቸው። ቢሆንም ከእያንዳንዳችን የራቀ አይደለም። ከናንተ ከባለ ቅኔዎች አንዳንዶች ደግሞ እኛ ደግሞ ዘመዶቹ ነንና ብለው እንደተናገሩ በእርሱ ሕያዋን ነንና እንንቀሳቀሳለን እንኖርማለን። እንግዲህ የእዚአብሄርን ዘመዶች ከሆንን አምላክ በሰው ብልሃትና አሳብ የተቀረፀውን ወርቅ ወይም ብር ወይም ድንጋይ እንዲመስል

እናስብ ዘንድ አይገባንም። እንግዲህ እጋዚአብሄር ያለማወቅን ወራት አሳልፎ አሁን በየቦታቸው ንሠሃ ይገቡ ዘንድ ሰውን ሁሉ ያዛል ቀን ቀጥሯልና። በዚያም ቀን ባዘጋጀው ሰው እጅ በዓለሙ ላይ በፅድቅ ሊፈርድ አለው” አለ (የሐዋሪያት ሥራ 17፡16~31)

አሁን ጳውሎስ ለአቴና ሰዎች የጣኦት አምልኮ እንዳጋጠመው አስተውለሃል ባለማወቅ እንደሚደረግ በማሳየት አውግዞታል። ከዚያም እውነተኛውን ስለ ህያው አምላክ እየሰበከላቸው ሄደ።

እነሱ ለምን ጣኦትን ያመልካሉ? ለምን እያንዳንዱ ለጣኦት ይንበረከካል? ጣኦት ማለት ከድንጋይ ከእንጨት ከብረት የተሠራ ነው።ነገር ግን ህይወት የለሽ ነው።መንፈስም የለሽ ነው። አያይም አይሰማም አያሽትም አይቀምስም አይንቀሳቀስም ወይም አይባርክም

ምንም እንኳን እንዲህ ያለው ነገር የሌላ ነገርን ወይም አንድን ግለሰብ ይወክላል ተብሎ በሚታሰብበት ጊዜ እንኳን በመጨረሻ “አምላክ” ተብሎ የሚታየው ጣኦቱ ነው።

ነገር ግን እነዚህ ህያው እግዚአብሄርን የማያውቁት ናቸው። ለጣኦት የሚሰግዱ ወይም ለሆነ ተፈጥሮ ወይም ለሰው ወይም ለሙታን የሚሰግዱት የሰማይ አምላክ ህያውን ባለምወቃቸው ነው።

አሁን እንደየዚያን ጊዜ በዓለም ዙሪያ ሰዎች ጣኦትን በማምለክ ቀጥለዋል። ግን ለምን?

ችግሩ በተመሳሳይ አለምወቅ መሆኑ ግልፅና የታወቀ ነው ከክርስቲና ውጭም ሆነ ክርስቲና በሚባለው ውስጥ ማንም አስተዋይ እና እውቀት ያለው ሰው ለጣኦት ወይም ለምሥል አይሰግድም

2. ቅዱሳት መጻህፍት ስለከንቱ አምልኮ ይናገራሉ

ኢየሱስ ሲናገር “የሰውም ሥርዓት የሆነ ትምህርት እያስተማሩ በከንቱ ያመልኩኛል” (ማቴዎስ 15፡9) ደግሞም እንዲህ አለ “በስማያት ያለውን የአባቴን ፈቃድ የሚያደርግ እንጂ ጌታ ሆይ ጌታ ሆይ የሚለኝ ሁሉ መንግስተ ሰማይ የሚገባ አይደለም በዙያ ቀን ብዙዎች ጌታ ሆይ ጌታ ሆይ በስምህ ትንቢት አልተናገርንምን? በስምህስ አጋንንትን አላስወጣንምን? በስምህስ ብዙ ተአምራትን አላደረግንምን ? ይሉኛል በዚያን ጊዜም ከቶ አላውቅኳቸሁም እናንተ አመፀኞች ከእኔ ራቁ ብየ እመስክርባቸሀዋለሁ” አለ (ማቴዎስ 7፡21~23)

አሁንም የጌታ ሰዎች በተለያየ መንገድ እንዲያመልኩ በአደባባይ እየተነገረ ነው። እናም በእሱ ውስጥ ታማግ እና ቅን እስከሆኑ ድረስ አምልኮታቸው በእግዚአብሄር ዘንድ ተቀባይነት ይኖረዋል የሚሉ አሉ። ይህ እውነት አይደለም እንደሰው ትምህርት እና ትዕዛዝ ከሆነ አምልኮው ከንቱ ነው። እንዲህ ዓይነት አምልኮ በጌታ ዘንድ ፈፁም ተቀባይነት አይኖረውም

የሰዎች ስብስብ “በክርስቶስ ስም” ስለተገናኙ ብቻ ይህ አምልኮ

ተቀባይነት ይኖረዋል ማለት አይደለም። በመጀመሪያ ደረጃ የሃይማኖት ድርጅት ቤተክርስቲያን አባል ሆነው የሚሰበሰቡ ከሆነ በክርስቶስ ስም ሳይሆን በቤተእምነታቸው ስም የሚሰበሰቡ ናቸው። ቀጥለው ደግሞ እንደቤተእምነታቸው አምልኳቸው በድርጅቱ መሰረት ይከናወናል። ጌታ ብዙ ሰዎች በፍርድ ቀን በፊቱ  እና ያደረጉትን ሁሉ ይናግራሉ ይላል። ነገር ግን ፈቃዱን ስላልታዘዙ እናም የቤተሰቡ አባልም ስላልሆኑ ከዚያም ይወቅሳቸዋል ይጥላቸዋል።

አምልኮህ እንደ ሰው ትምህርት ከሆነ ማለትም በእግዚአብሄር ቃል ውስጥ የማታገኘውን በአምልኮ ውስጥ እያደርጋቸው ነው። እንግዲህ አምልኮህ ከንቱ ነው ስለዚህም ብጌታ ዘንድ ተቀባይነት አይኖረውም ስለዚህ ያንተን ሁኔታ ለመመርመር ጊዜው አሁን ነው።

3. ቅዱሳት መጻህፍት ስለ እውነተኛ አምልኮ ይናገራሉ

ክርስቶስ ሲናገር "እግዚአብሄር መንፈስ ነው የሚሰግዱለትም በመንፈስና በእውነት ሊሰግዱለት ያስፈልጋቸዋል" ይላል (ዮሃንስ 4፡24)

አሁን እዚህ ጋ ጥቂት ነገሮችን እናስተውል በመጀመሪያ ቀደም ባለው ትምህርት እንዳጠናነው እግዚአብሄር የአምልኮታችን አካል ወይም ግብ መሆን አለበት ፡፡ ሁለተኛ እርሱን የሚያመልኩት ብጌታ ቃል መሰረት ማድረግ አለባቸው። ማንም ሰው እግዚአብሄርን ለማምለክ አይገደድም ነገር ግን ይህን ለማድረግ የመረጡት በጌታ ቃል ይሁን እንጂ አምልኮው በእሱ ለእሱ መሆን አለበት ሦስተኛ አምልኮው በመንፈስ እና በእውነት መከናወን አለበት ምን ማለት ነው? በቀላሉ አምልኳችን በቅንነት ለማስተዋል እና በተሰበረ መንፈስ መሆን አለበት ማለት ነው። እውነትን በተመለከተ አምልኳችን መጽሀፍ ቅዱስ ውስጥ በተጻፈው እውነት መሰረት መሆን አለበት። በቅዱሳት መጽሀፍ እንደተጻፈው አሁን ቀላል አይደለም? ለአንዳንዶች ግን በጣም ቀላል ነው እነሱ ሁሉንም ዓይነት የአምልኮ ሥራቶችን እና የመሳሰሉትን ማለፍ ይፈልጋሉ። ግን ጌታ የሚፈልገው ያን አይደለም።ሕዝቡ በታዘዘው መሰረት ከልባቸው እንዲያመልኩት ይፈልጋል። ሳይጨምሩ ሳይቀንሱ እንደ ቃሉ ማለት ነው።

ይህ በአዲስ ኪዳን የተማርነው አምልኮ ነው። በትምህርታችንም ስንቀጥል የጥንቶቹ ክርስቲያኖች በዚህ መልኩ ያመልኩ እንደነበር እና እኛም ማምለክ ያለብን በዚህ መንገድ መሆኑን ማወቅ አለብን። ሁላችንም ይህን ነገር ስናደርግ በአንድነት እንሰግዳለን ጌታም አምልኳችንን ይቀበላል።

**ጥያቄዎች**

1. በአዲስ ኪዳን ውስጥ ስንት ዓይነት አምልኮዎች አነበብን?
2. ይህን ያጠናንበትን ምክንያት ጥቂት ጥቀስ
3. ጳውሎስ የአቴንስ ከተማ እንዴት ሆና አገኛት?

4. የአቴንስ ሰዎች ያመልኩ የነበረው ምን ዓይነት ነበር?
5. ጳውሎስ ስለዚያ አምልኮ ምን አለ?
6. ጳውሎስ ሰዎቹን ወደ ምን ምን ብሎ እንደጠቆማቸው ጥቀስ
7. ወዴት ነው የጠቆማቸው?
8. እነሱ ለምን ጣኦታትን ያመልካሉ?
9. ጣኦታት ከምን ከምን የተሰሩ ናቸው?
10. ጣኦታት ሊያደርጉ የማይችሉትን ጥቂት ጥቀስ
11. ህያው አምላክን የሚያውቅ ለጣኦት ይሰግዳል?
12. ዛሬስ ጣኦታትን የሚያመልኩ አሉ?
13. ማቴዎስ 15፡9 ጥቀስ
14. ማቴዎስ 7፡21~23 አንብብ
15. ከንቱ አምልኮ ምንድነው?
16. "በክርስቶስ ስም" ስለተሰበሰቡ ብቻ አምልኳቸውተቀባይነት ይኖረዋል?
17. ጌታ የሚፈልገው አምልኮ ምን ዓይነት ነው?
18. የአምልኮአችን ግብ ማን መሆን አለበት?
19. ጌታ ሰዎች እንዲያመልኩት ያስገድዳል?
20. በማን ውል ነው አምልኮ ሊፈፀም የሚገባው?
21. እግዚአብሄርን በመንፈስና በእውነት ማምለክ ምን እንደሆነ ግለፅ፡፡

## ትምህርት አምሥት
## የጥንቶቹ ክርስቲያኖች አምልኮ

ሰዎች እንዴት እንደሚያመልኩ ምን እንደሚያመልኩ መቼ እንደሚያመልኩ ሲያመልኩ ምን እንደሚያደርጉ ማወቅና ማስተዋል በጣም አስደሳች ነው፡፡ በዘመናችን ብዙ አብያተክርስቲያናት በተለያዩ መንገድ እያመለኩ እንደሆነ እናውቃለን፡፡ ግን ለምን ልዩነት ሆነ? ሊዩነት ሊኖር ይገባ ነበር? እኛስ ጌታ እንደሚፈልገው እያመለክን መሆናችንን እንዴት እናውቃለን? ይህን ለማወቅ የተሻለ መንገድ የሚሆነው ወደ መጽሃፍ ቅዱስ በመሄድ የጥንቶቹ ክርስቲያኖች እንዴት እንዳመለኩ ማየት ነው፡፡

በጴንጤቆስጤ ቀን ቤተክርስቲያን ከተመሰረተች ብኃላ ቃሉ እንደሚነግረን "በሓዋሪያትም ትምህርት በህብረት እንጀራውንም በመቁረስ በየፀሎቱም ይተጉ ነበር" (ሓዋሪያት ሥራ 2፡42) እነዚህ ደቀመዛሙርት ወይም ክርስቲያኖች በሓዋሪያት ትምህርትም ይተጉ እንደነበር እናያለን፡፡ ምን አደረጉ? ሁሉም አምልኮ በዚህ ጥቅስ ውስጥ ባይነገርም እዚህ ቦታ ሦስት ተጠቅሷል ኅብረት ስጦታ እንጀራን መቁረስ እና በፀሎት በመትጋት ያመልኩ ነበር፡፡

በኃላ ላይ ጳውሎስ በጉዞው ላይ ጢሮአዳ ሲያልፍ የሆነውን ስናነብ “ከሳምንቱ በመጀመሪያ ቀን እንጀራ ለመቁረስ ተሰብስበን ሳለን ጳውሎስ በነገው ሊሄድ ስላሰበ ከእነርሱ ጋር ይነጋገር ነበር። እስከ መንፈቀ ሌሊትም ነገሩን አስረዘመ” (የሓዋሪያት ሥራ 20:7) እዚህ ላይ የምናስተውለው የአምልኮው ቀን ከሳምንቱ የመጀመሪያ ቀን መሆኑን ነው።

ጳውሎስ ሰኞ ላይ እንደደረሰ ግልፅ ነው። ነገር ግን ከእነሱ ጋር የማምለክ ዕድል ለማግኘት ከዚያም ሣምንቱን ቆየ እና ቅዳሜንም በማለፍ የሣምንቱ የመጀመሪያ ቀን እንደሚመጣ እና ከጌታ ሰዎች ጋር ለማምለክ ይችል ዘንድ። ከዚያም በተጨማሪ ደቀመዛሙርቱ ወይም ክርስቲያኖች እንጀራ ለመቁረስ ወይም የጌታን እራት በመካፈል የተሰበሰቡበት በዚህ ቀን እንደሆነ ነው። በመጨረሻም ጳውሎስ ይህን አጋጣሚ ተጠቅሞ ሰበከላቸውና በኃላም መንገዱን ቀጠለ።

በ1ኛ ቆሮንቶስ 10 እና 11 ላይ ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ወንድሞች ስለጌታ እራት አስፈላጊነት የጻፈውን ስናነብ እስቲ እናስተውል “ለናንተ ደግሞ አሳልፌ የሰጠሁትን እኔ  ከጌታ ተቀብዬአለሁና ጌታ ኢየሱስ አልፎ በተሰጠባት በዚያች ሌሊት እንጀራን አንስቶ አመሰገነ ቆርሶም እንካችሁብሉ ይህ ስለናንተ የሚሆን ሥጋዬ ነው ይህን ለመታሰብያዬ አድርጉት አለ። እንደዚሁም ከእራት በኃላ ፅዋውን አንስቶ ይህ ፅዋ በደሜ የሚሆን የአዲስ ኪዳን ነው በጠጣቻሁት ጊዜ ሁሉ ይህን ለመታሰቢያዬ አድርጉት አለ። ይህን እንጀራ በበላቻሁት ጊዜ ሁሉ ደንም ፅዋ በጠጣቻሁት ጊዜ ሁሉ ጌታ እስኪመጣ ድረስ ሞቱን ትናገራላችሁና። ስለዚህ ሳይገባው ይህን እንጀራ የበላ ወይም የጌታን ፅዋ የጠጣ ሁሉ የጌታ ሥጋና ድም ዕዳ አለበጥ ሰው ግን ራሱን ይፈትን እንዲሁም ከእንጀራው ይብላ ከፅዋውም ይጠጣ። ሳይገባው የሚበላና የሚጠጣ የጌታን ሥጋ ስለማይለይ ለራሱ ፍርድ እበላልና ይጠጣልምና። ስለዚህ በአንዳንድ ዘንድ የደከሙና የታመሙ ብዙዎች አሉ አያሌዎችም አንቀላፍተዋል። ራሳችንን ብንመረምር ግን ባልተፈረድብንም ነበር። (1 ኛ ቆሮንቶስ 11፡23~31)። እስቲ እንመልከት

1. ጳውሎስ ይህንን የተቀበለው ከጌታ ነው
2. የሚናገረው እንጀራው የጌታን ሥጋ ፅዋው የጌታን ደም እንደሚወክል ነው።
3. ይህንንም የሚካፈሉት ለጌታ ሥጋና ደም መታሰቢያ ነው
4. ይህንን ሲያደርጉ ጌታ እስከሚመጣ ድረስ ሞቱን ይናገራሉ
5. ሳይገባቸው ይህንን የሚበሉና የሚጠጡ የጌታ ሥጋና ደም ባለዕዳ ናቸው። ይህንም ሳይገባቸው መውሰድ አደጋ እንዳለው ይገልጻል።
6. ይህንን ከመውሰዳቸው ብፊት መንፈሳዊ ህይወታቸውን ምን እንደሚመስል ራሳቸውን መመርመር እንዳለባቸው ያስረዳል። ይህ ማለት ሃሳቡ ምናልባት በኃጥያት ውስጥ ከሆኑና በዚህ ምክኛት የመውሰድ

ቋመና ከሌላቸው ከመውሰዳቸው በፊት በንሰሃ ከጌታ ጋር መስማማት እንዳለባቸሀውና ከዚያ ቦኃላ መውሰዱን እንዲቀጥሉ ነው፡፡ ወደ ጌታ ለመቅረብ መወገድ ያለበትን አስወግዶ ታማኝ ክርስቲያን በመሆን ለመውሰድ እራስን ማዘጋጀት ማለት ነው፡፡

7. ጳውሎስ እያንዳንዱ ሰው ከመካፈሉ በፊት እራሱን መመርመር አለበት ብሎ እስካለ ድረስ የጌታ ሰዎች የተዘጋ ህብረት መመስረት የለባቸውም፡፡ እግዚአብሄር ልብን ማየት ይችላል እኛ ግን እንደቤተክርስቲያን አባላት በስው ላይ የመፍረድ መብት የለንም፡፡ ነገር ግን መጻፍ ቅዱስ ከሚያስተምረው አንፃር የራሱን ጉዳይ ማጤን የግለሰቡ ድርሻ ነው፡፡

ደግሞም በ 1ኛ ቆሮንቶስ 11 ጳውሎስ የጌታ እራት ግብዣ ስላደረጉና በዚህ መሳለቂያ በማድረግ የቆሮንቶስን ሰዎች አውግዞአቸዋል፡፡ የሚበሉበትና የሚጠጡበት የራሳቸው ቤት እንዳላቸውና ለአምልኮ በሚሰበሰቡበት ጊዜ ለመብላትና ለመጠጣት ዓላማው ለአካል ወይም ሰውነት መሙላት መሆን እንደሌለበት ጠቁሟል፡፡ ዛሬም ቢሆን በተመሳሳይ ነው፡፡ ክርስቲያኖች በቁምነገር ተገናኝተው ማምለክ አለባቸው፡፡ የክርስቶስን ሥጋና ደም በማሰብ ብቻ ከኅብረቱና ከፅዋው ይካፈሉ እንጂ ሌላ ምንም ሊሆን አይችልም፡፡

ከዚያ ወደ 1 ኛ ቆሮንቶስ 16፡1~2 ስንመለስ በዚሁ ተመሳሳይ ፀሃፊ ጳውሎስ ከስጦታ ጋር እናገኘዋለን፡፡ እንዲህ ይላል "ለቅዱሳኖች ገንዘብ ስለ ማዋጣት ለጋላቲያ አብያተክርስቲያናት እንደደነገግኩት እንዲሁ አድርጉ፡፡ እኔ ስመጣ ይህ የገንዘብ ማዋጣት ያን ጊዜ እንዳይሆን ከናንተ እያንዳንዱ በየሳምንቱ በፊተኛው ቀን እንደቀናው መጠን እያስቀረ በቤቱ ያስቀምጥ" (1ኛ ቆሮንቶስ 16፡1~2)፡፡ ቀጥሎም እንዲህ ይላል "ይህንም እላለሁ በጥቂት የሚዘራ በጥቂት ደግሞ ያጭዳል በበረከት የሚዘራ በበረከት ደግሞ ያጭዳል፡፡ እግዚአብሄር በደስታ የሚሰጠውን ይወዳልና እያንዳንዱ በልቡ እንዳሰበ እስጥ በሃዘን ወይም በግድ አይሁን " (2 ቆሮንቶስ 9፡6~7) በእርግተኝነት የእግዚአብሄር ህዝብ እንዲሰጡ የጠበቅባቸዋል፡፡ ከዚህ በታቾ እስቲ እንመልከት

1. በሳምንቱ የመጀመሪያ ቀን ማድረግ አለባቸው
2. ሁሉም ክርስቲያኖች መስጠት አለባቸው
3. በልባቸው ያሰቡትን መስጠት አለባቸው
4. የሚሰጡት በተባረኩበት መጠን መሆን አለበት ዬትም ቦታ ግን በአዲስ ኪዳን አስራት ወይም በኩራት ወይም ይህን ያህል የተባለ የለም
5. ሊሰጡ የሚችሉት እንደቀናቸው መጠን ወይም ሊሰጡ በልባቸው እንዳሰቡት ነው
6. ሲሰጡ በግድ ወይም በሃዘን መሆን የለበትም
7. ይልቁንም በደስታ ደስ እያላቸው ሊሰጡ ይገባል ምክንያቱም

እግዚአብሄር በደስታ የሚሰጡትን ይወዳልና

በአዲስ ኪዳን ውስጥ ስለመዝሙር ብዙ ተጠቅሷል እና ጳውሎስና ሲላስ በእስር ቤት እያሉ እግዚአብሄርን ያመሰኑ ነበር (ሐዋሪያት ሥራ 16፡ 25) ነገር ግን የጌታ ህዝብ ጉባኤ ላይ በተሰበሰቡበት ዘመሩ የሚል ምሳሌ የለም ሆኖም ግን በመንፈስ ቅዱስ መሪነት የጻፈ ሃዋሪያ መዝሙርን አዟል (ኤፌሶን 5፡19፤ ቆላስያስ 3፡16) ስለዚህም በመጀመሪያው ክፍለዘመን የነበሩ ክርስቲያኖች ያካሄዱት ሌላው የአምልኮ ሥራዓት መዝሙር ነው፡፡
እንግዲህ ሁሉንም በአንድ ላይ ስናይ የእግዚአብሄር ሰዎች በሳምንቱ የመጀመሪያ ቀን የሰበሰባሉ በዚህ ቀን ይፀልያሉ የእግዚአብሄርን ቃል ያጠናሉ፤ ይዘምራሉ፤ የጌታ እራት ወይም ቅዱስ ቁርባን ይወስዳሉ ስጦታን ይሰጣሉ፡፡ ከዚህ ውጪ አንዳች የአምልኮ ሥርዓት አልተጻፈም፡፡

## ጥያቄዎች

1. አብዛኞቹ አብያተክርስቲያናት አምልኮአቸው ተመሳሳይ ነው?
2. እኛ ጌታ እንደሚፈልግ እያመለክን መሆናችንን እንዴት ልናውቅ እንችላለን?
3. በጴንጤቆስጤ ቀን ቤተክርስቲያን ከተመሰረተች ቦኃላ ምንድነው የሆነው?
4. ሐዋሪያት ሥራ 2፡42 ትቀስ
5. ደቀመዛሙርቶች በምን ነበር የቀጠሉት?
6. በሁሉም የአምልኮ ሥርዓት በዚህ ጥቅስ ተጠቅሷል?
7. ጳውሎስ በጢሮአዳ ለጥቂት ቀናት የቆየው ለምንድነው?
8. ሐዋሪያት ሥራ 20፡7 ምን ይላል?
9. ከሳምንቱ በዬትኛው ቀን ክርስቲያኖች ይሰበሰባሉ?
10. ሲሰበሰቡ እነሱ የሚያደርጉትን ጥቂት ግለፅ
11. ክርስቲያኖች እነማን ናቸው?
12. ጳውሎስ ከጌታ የተቀበለው ምንድነው?
13. ለምንድነው የጌታን ሥጋና ደም የሚወስዱት?
14. ይህ ምንን ያመለክታል?
15. ሰው ሳይገባ እንዴት ይወስዳል?
16. “ሰው መጀመሪያ ራሱን ይመርምር” የሚለው ምን ማለት እንደሆነ ግለፅ
17. አንድ ሰው እራሱን ለመጉዳት መውሰድ አለበት?
18. ታማኝ ክርስቲያን ሆኖ የጌታ እራትን አለመውሰድ ይቻላል?
19. የእግዚአብሄር ሰዎች በተዘጋ የጌታ እራት መውሰድ ይችላሉ?
20. ጳውሎስ የቆሮንቶስ ሰዎች የጌታ እራት አወሳሰዳቸው ላይ ለምን አወገዛቸው?

21. 1ኛ ቆሮንቶስ 16፡1~2 አንብብ

22. በዬትኛው ቀን ነው ክርስቲያኖቸህ ገንዘብ ማዋጣት የሚችሉት?

23. ስንት ወይም ምን ያህል ይሰጣሉ?

24. ምንድነው ይሰጡ የነበረው?

25. ሊሰጡ የሚገባቸህው መጠን ግለፅ

26. 2 ቆሮንቶስ 9፡6~7 ጥቀስ

27. እግዚአብሄር እንዴት ኣይነት ሰጪ ይወዳል?

28. አምስቱን የአምልኮ ሥርዓት ዘርዝር

## ትምህርት ስድስት
## የአምልኮ ቀን

በአዲስ ኪዳን ውስጥ የምንማረው ስለአምልኮ አስፈላጊነት ብቻ አይደለም፡፡ ነገር ግን ጌታ ህዝቦቸሁ በዬትኛው `እንዲያመልኩት እንደሚጠብቅባቸውም ጭምር እንጂ፡፡ ይህ ቀን መቼ ነው?

አሁንም የሰንበት ቀን በሰው ላይ እንደአምልኮ ቀን ነ ብለው የሚያስተምሩ አሉ፡፡ ይህ እውነት ነው? ህጕ ከመንገድ እንደተወገደ በ 2 ኛ ቆሮንቶስ 3፣ ቆላስያስ 2፡14፣ ዕብራዊያን 9፡16~17፣ እና ዕብራዊያን 10፡9፣ ላይ እናነባለን፡፡ ጳውሎስ በሰንበት ቀን ከአይሁድ ጋር ቢገናኝም ተከርክሯል፡፡ ይህ እውነት ሊሆን ይችላል ፡፡ ለአምልኮ መገናኘቱን ግን ዬትም ቦታ አልተገለፀም፡፡ ወይም አናነብም፡፡ ይልቁንም የእግዚአብሄርን ቃል የማስተማር ዕድል እንዲያገኝ ከነሱ ጋር ተገናኘ፡፡

በሰንበት ቀን የአምልኮ ቀን አይደለም፡፡ ያ ካልሆነ የአምልኮ ቀን መቼ ነው? የአዲስ ኪዳን ገፆች ስንመለከት ለንዚህ ጥያቄዎች መልስ የሚሆኑ ካንድ በላይ የቅዱሳት መጽሃፍት ማጣቀሻዎች አሉን፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ ለአምልኮ የተሰበሰቡበትን የአዲስ ኪዳን ክርስቲያኖች ቡድን ምሳሌ እንወስዳለን፡፡ እና በዬትኛው ቀን እንደመረጡ እናያለን፡፡ ለምሳሌ ጳውሎስ በጢሮአዳ ከተማ ሲዘዋወር በአከባቢው ካሉት ክርስቲያኖች ጋር ለአምልኮ የመሰብሰብ አጋጣሚ ሊኖረው እንደሚችል ዘገባው ይናገራል እስቲ እናንብበው “ከሳምንቱም በመጀመሪያ ቀን እንጀራ ለመቁረስ ተሰብስበን ሳለን ጳውሎስ በነገው ሊሄድ ስላሰበ ከነርሱ ጋር ይነጋገር ነበር እስከመንፈቀ ሌሊትም ነገሩን አስረዘመ” (ሓዋሪያት ሥራ 20፡7) እባክህን የሓዋሪያት ሥራ 20፡6 ተመልከት በጢሮአዳ ሰባት ቀን እንደተቀመጠ አስትውል ይህም ማለት በሰንበት ወይም ቅዳሜም በዚያ ነበረ ማለት ነው፡፡ ነገር ግን ዘገባው እንደሚለን በዚህ ቀን ከክርስቲያኖች ጋር መገናኘቱን ምንም አይናገርም ይልቁንም በሣምንቱ የመጀመሪያ ቀን ወይም ከሰንበት ቀጥሎ በመጀመሪያው ቀን ነው፡፡ አሁን የዚህ ጠቀሜታ ምን ይሆን? ትርጕሙ በሰንበት ቀን አለመስገዳቸው ወይም አለማምለካቸው ነው፡፡ ይልቁንም

ጌታ ለአምልኮ በወሰነው ቀን እና በሣምንቱ የመጀመሪያ ቀን ለመስገድ እዚያ መገኘቱ ነው።

ለማንኛውም የሣምንቱ የመጀመሪያ ቀን ምንድነው? በህጉ መሠረት የሰንበት ቀን የሣምንቱ ሰባተኛ ቀን ነበር። ይህ ማለት ሰንበት የሣምንቱ ሰባተኛ ቀን ከሆነ እና በሳምንት ውስጥ ሰባት ቀናት ብቻ ካሉ ከዚያ ከሰንበት ቀጥሎ ወይም ከሰንበት በኃላ ያለው ቀን የሳምንቱ የመጀመሪያ ቀን ነው። በርግጥ በዘመናዊው አጠራር የሣምንቱ የመጀመሪያ ቀን እሁድ ብለን እንጠራዋለን። እሁድ ደግሞ የሣምንቱ የመጀመሪያ ቀን ተብሎ ይታወቃል።

ግን ለምን ከሣምንቱ የመጀመሪያ ቀን ሆነ? መልካም ! በሙሴ ህግ የአምልኮ ቀን በሰንበት ቀን ወይም ከሣምንቱ የመጨረሻ ቀን ወይም ሰባተኛ ቀን ነው። በክርስቶስ ህግ ውስጥ ደግሞ የአምልኮ ቀን በሳምንቱ የመጀመሪያ ቀን ወይም እሁድ ነው። ያ ማለት ጌታ የመጣው በመጀመሪያው ነው እንጂ የመጨረሻ አይደለም (ማቴዎስ 6፡33)

በሌላ በኩል ጥናታችንን ስንቀጥል ሓዋሪያው ጳውሎስ የቆሮንቶስ ወንድሞችን መመሪያ ሲሰጥ እንዲህ ይላል “ለቅዱሳንም ገንዘብን ስለማዋጣት ለገላቲያ አብያተክርስቲያናት እንደደነገግኩ እናንተ ደግሞ እንዲሁ አድርጉ። እኔ ስመጣ ይህ ገንዘብ ማዋጣት አይሁን ከእናንተ እያንዳንዱ በየሣምንቱ በፊተኛው ቀን እንደቀናው መጠን እያስቀረ ብቤቱ ያስቀምጥ “ (1 ኛ ቆሮንቶስ 16፡1~2) እንደቀናቸው መጠን እንዲሰጡ ይህ ቀን ለምን ተመረጠ? ምክያቱም ይሄ የአምልኮ ቀን ነው። እናም ለአምልኮ መሰባሰባቸው ስለማይቀር ስጦታውንም በዚያው እንዲያደርጉ ተብሎ ነው።ሰንበት ወይም ሰባተኛ ቀን ቢሆን ኖሮ ጳውሎስ የፊተኛው ቀን ብሎ ባልተናገረ ነበር። እንግዲህ እነዚህ ሰንበት ወይም ሰባተኛ ቀን የአምልኮ ቀን ነው የሚሉት በ1ኛ ቆሮንቶስ 16፡1~2 ላይ የተጻፈውን ለመፈጸም እንደገና በነጋታው ይመጣሉ ማለት ነው? ካል ሆነስ ለምን ?

በኃላ ላይ ዮሃንስ ስለዚህ የሣምንቱ የመጀመሪያ ቀን ሲናገር እንዲህ ይላል “እኔም በጌታ ቀን በመንፈስ ነበርኩ” (ዮሃንስ ራዕይ 1፡10) በርግጥ ሁሉም ቀኖች የጌታ ቀኖች ናቸው። ነገር ግን ዮሃንስ ይህንን ሲገልፅ በልዩ ሁኔታ ነው። እነዚህ የአምልኮ ቀን በመንፈስ የሚኮንበት ቀን የሣምንቱ የመጀመሪያ ቀን ባይሆን ኖሮ እንዴት የጌታ ቀን ይላል?

ነገር ግን ለምን የሣምንቱ የመጀመሪያ ቀን አስፈላጊ ሆነ? ቀደም ሲል እንደተገለፀው እሱ የሕጎችን ለውት የሚጠቁም  እና  ሌሎች በርካታ ምክንያቶች አሉ።

1. ክርስቶስ ከሣምንቱ የመጀመሪያ ቀን ከመቃብር ተነሣ

በጌታ ትንሳኤ ማለዳ ዘገባው እንዲህ ይላል “በሰንበትም መጨረሻ መጀመሪያ ቀን ሲነጋ መግደላዊት ማሪያምና ሁለተኛይቱ ማሪያም

መቃብሩን ሊያዩ መጡ” (ማቴዎስ 28፡1) ከትንሽ ቀናት በኃላም እንዲህ የሚል እናነባለን “ያም ቀን እርሱም ከሣምንቱ ብፊተኛው በመሸ ጊዜ ደቀመዛሙርቱ ተሰብስበው በነበሩበት አይሁድን ስለፈሩ ደጆቹ ተዘግተው ሳሉ ኢየሱስ መጣ በመካከላቸውም ቆሞ ሰላም ለናንተ ይሁን አላቸው” (ዮሃንስ 20፡19)

2. ኢየሱስ በድጋሚ በሣምንቱ የመጀመሪያ ቀን ለደቀመዛሙርት ታየ

ኢየሱስ በሣምንቱ የመጀመሪያ ቀን ከመቃብር መውጣቱ እና በዚያው ቀን ለደቀመዛሙርቱ መገለጡ ብቻ ሳይሆን ዳግም በሣምንቱ ደግሞ እንደገና መታየቱን ማወቁ ጠቃሚ ነው፡፡ እንዲ ይላል “ከስምንት ቀን በኃላም ደቀመዛሙርቱ ደግመው በውስጥ ነበሩ ቶማስም ከእነርሱ ጋር ነበረ፡፡ ደጆች ተዘግተው ሳሉ ኢየሱስ መጣ በመካከላቸውም ቆሞ ሠላም ለእናንተ ይሁን አላቸው” (ዮሃንስ 20፡26) ኢየሱስ ከሳምንቱ የመጀመሪያው ቀን ለደቀመዛሙርቱ ተገለጠ እናም ክስምንት ቀን በኃላ ደግሞ ድጋሚ ከታያቸው ሁለተኛው ጉብኝት መቼ መሆኑ ነው? ከሣምንቱ የመጀመሪያ ቀን ነው፡፡ ቅዱሳት መጻህፍት ለምን ደጋግመው በዚህ ቀን እንድናተኩር ፈለጉ? ምክንያቱም ይህ ቀን በክርስቶስ ሕግ ውስጥ አስፈላጊ ቀን በመሆኑ ነው፡፡ የአምልኮ ቀንም እንዲሆን ነው፡፡

3. ቤተክርስቲያንም የተጀመረው ከሣምንቱ የመጀመሪያ ቀን ነው (ሓዋሪያ ሥራ 2)

የጴንጤቆስጤ ቀን የሚመጣው ከፋሲካ በሃምሳኛው ቀን ነው፡፡ይህም ኢየሱስ ከመቃብር የተነሳበት ቀን ነው፡፡ ኢየሱስ ከሣምንቱ የመጀመሪያ ቀን ከመቃብር ከተነሣ እና የጴንጤቆስጤ ቀን በሃምሳኛው ቀን ከሆነ የጴንጤቆስጤ ቀን መቼ ነው? ከሳምንቱ የመጀመሪያ ቀን ነው፡፡ ነገር ግን የጴንጤቆስጤ ቀን አስፈላጊነት ምንድነው? በዚህ ጉዳይ ላይ በሣምንቱ የመጀመሪያ ቀን መምጣቱ አስፈላጊ ነው፡፡ ይህም የጌታ ቤተክርስቲያን የተመሰረተበት ቀን ነበር፡፡ እንዲያ ብቻም አይደለም በዚህ ቀን ለመጀመሪያ ጊዜ ብዙ አስፈላጊ ነገሮች ተከስተዋል፡፡ እነዚህ ሁሉ ነገሮች በዚህ ልዩ ቀን ላይ የበለተ ትኩረት ይሰጣሉ፡፡ ለምሳሌ መንፈስ ቅዱስ በዚህ ቀን ወረደባቸው፡፡ የመጀመሪያው ወንጌል በዝሁ ቀን ተሰበከ፡፡ የመጀመሪያዎቹ ይታዘዙት ነፍሳት የዳኑበት ቀን ነው፡፡ በዚህ ቀን የዳኑት በዚሁ ቀን ወደ ቤተክርስቲያን ተጨመሩ፡፡ ስለዚህ እነዝህ ነገሮች የተከስተቱበት ቸላ ተብሎ የሚታለፍ አይደለም፡፡

ጌታ የሣምንቱን የመጀመሪያ ቀን ህዝቡ የሚሰበሰብበትን ለእሱ የሚሰግዱበት ቀን እንዲሆን እንደመረጠ አሁን እርግተኞች ነን፡፡ የጥንቶቹ ክርስቲያኖች በዚህ ቀን ሲሰበሰቡና ከዚያም በዚህ ቀን እንዲሰበሰቡ ሲታዘዙ ሁሉንም ጥርታሬዎቸን ያስወግዳል፡፡ ጌታ በአምልኮና በሌሎቸ ነገሮች ሁሉ ቀዳሚ መሆኑን አስታውስ፡፡ ለዚያም ነው ክርስቲያኖች

በያንዳንዱ የመጀመሪያ ቀን ሲሰበሰቡና ለእነርሱ የሞተውንና በሣምንቱ የመጀመሪያ ቀን ለእነርሱ የተነሳውን  ጌታ ለማምለክ ለማሰብ ይሰበሰባሉ

## ጥያቄዎቾ

1. የአምልኮ ቀን አስፈላጊ ነው?
2. ጌታ ህዝቡ እንዲሰግድለት የሚጠብቅበትን ቀን ወስኗል?
3. የሰንበት ቀን አሁንም ፀንቶ ነው ያለው?
4. 2 ቆሮንቶስ 3፣ ቆላስያስ 2፡14፣ ዕብራዊያን9፡16~17፣ ዕብራዊያን 10፡9፣ እና ሉቃስ 24፡44 ምን ያስተምራሉ?
5. ጳውሎስ ከአይሁዶች ጋር በሰንበት ቀን የተገናኘው ለምንድነው?
6. በሓዋሪያት ሥራ 20፡7 ክርስቲያኖች የተሰበሰቡት በምን ቀን ነበር?
7. የሰንበት ቀን የአምልኮ ቀን ከሆነ ደቀመዛሙርት ለምን የሳምንቱ የመጀመሪያ ቀን ትተው በሰንበት አልተሰበሰቡም?
8. የሣምንቱ የመጀመሪያ ቀን ምንድነው?
9. የሣምንቱ የመጀመሪያ ቀን ለን የአምልኮ ቀን ተብሎ ተመረጠ?
10. የቆሮንቶስ ክርስቲያኖቸህ የሚሰበሰቡበትና ስጦታ የሚሰጡበት ቀን መቼ እንደሆነ ተናገር
11. የጌታ ቀን የሚለውን አብራራ
12. የሣምንቱ የመጀመሪያ ቀን ለምን አስፈላጊ ሆነ?
13. ኢየሱስ ከመቃብር የተነሣው በዬትኛው ቀን ነው?
14. የጴንጤቆስጤ ባዓል የመጣው በዬትኛው ቀን ነበር?
15. በዚያ በ ጴንጤቆስጤ ቀን የተከሰቱትን ነገሮች ዘርዝር

## ትምህርት ሰባት
## የአምልኮ ሥርዓት

በዘመናቸን የሃይማኖት ዓለም ብዙ ዓይነት አምልኮዎች አሉ። ካቶሊኮች ኦርቶዶክሶች ፕሮተስታንቶች ሁሉ የየራሳቸው የተለያዩ የአምልኮ ሥርዓት አላቸው። ይህ ማለት የተለያዩ የአምልኮ ሥርዓቶችን ወደ ሚለያዩበት ሳምንታት እና ሳምንታትን ማሳለፍ ይቸላሉ ማለት ነው። ግን ለምን? ጌታ የቀደው ወይም የፈለገው በዚህ መንገድ ነውን ?

መጽሃፍ ቅዱስ ሲያስተምር ቤተክርስቲያን አንድ ብቻ ናት እርስዋም የጌታ ናት (ኤፌሶን 4፡4፣ ማቴዎስ 16፡18) ስለቤተክርስቲያን አምልኮ ሥርዓት ያለው በአዲስ ኪዳን ውስጥ ብቻ ነው። ይህ እውነት ነው። እንግዲህ ቤተክርስቲያን የጌታ ከሆነቸና እንድታመልክ ደግሞ ከታዘዘቸ ሥርዓቱ እዚያ ነው ማለት ነው

እንግዲህ ጌታ ሕዝቦቹ እንዴት አድርገው እንዲያመልኩት ለማወቅ

ወደ አዲስ ኪዳን መሄድና ማጥናት አለብን። ከዚያ ውጪ ልንውቅ የምንችልበት ሌላ ምንም መንገድ የለም። ይህን የምንመረምረውም በትክክል ለአምልኮ ጊዜ ማድረግ ያለብንን ጌታ ከእኛ የሚፈልገውን ለማረጋገጥ ይሆናል።

1. እግዚአብሄር ሊመለክ የሚገባው አምላክ ነው።

ክርስቶስ በስይጣን በተፈተነበት ጊዜ እንዲህ አለ። “ሂድ አንተ ሰይጣን ለጌታህ ለአምላክህ ስገድ እርሱንም ብቻ አምልክ ተብሎ ተፅፎል” አለው (ማቴዎስ 4፡10)

2. የአምልኮ ቀን በሣምንቱ የመጀመሪያ ቀን ነው

ደቀመዛሙርት በሣምንቱ የመጀመሪያ ቀን እንዲሰበሰቡ ታዘዋል “እኔ ስመጣ ይህ ገንዘብ ማዋጣት ያን ጊዜ እንዳይሆን ከእናንተ እይንዳንዱ በየሣምንቱ ብፊተኛው ቀን እንደቀናው መጠን እያስቀረ በቤቱ ያስቀምጥ” (1 ኛ ቆሮንቶስ 16፡2)

3. ክርስቲያኖች ጌታን ያመልካሉ

ለዚህ ምሣሌ አለን “በሐዋሪያት ትምህርት እንጀራንም በመቁረስ በኅብረት በየፀሎትም ይተጉ ነበር” (የሐዋሪያት ሥራ 2፡42) ከሣምንቱም በመጀመሪያ ቀን እንጀራን በመቁረስ ተሰብስበን ሳለን ጳውሎስ በነገው ሊሄድ ስላሰበ ከነርሱ ጋር ይነጋገር ነበር። እስከ መንፈቀ ሌሊትም ነገሩን አስረዘመ “ (የሐዋርያት ሥራ 20፡7)

4. እንዴት እንደምናመልክ ተነግሮናል

ክርስቶስ ሲናገር “ነገር ግን በእውነት የሚሰግዱ ለአብ በመንፈስና በእውነት የሚሰግዱበት ጊዜ ይመጣል አሁንም ሆኗል። አብ ሊሰግዱለት እንደነዚህ ያሉትን ይሻልና እግዚአብሄር መንፈስ ነው የሚሰግዱለትም በመንፈስና በእውነት ሊሰግዱለት ያስፈልጋቸዋል” (ዮሐንስ 4፡23~24)

5. አምስቱ የአምልኮ ዓይነቶች ተዘርዝረዋል

እነሱም የሚያጠቃልሉት መጽሐፍ ቅዱስን ማጥናት (2 ኛ ጢሞቴዎስ 2፡15) ፀሎት (የሐዋሪያት ሥራ 2፡42) መዘመር (ኤፌሶን 5፡19)፣ የጌታ እራት መካፈል (ማቴዎስ 26፡26~28) እናም ስጦታ ናቸው (2ኛ ቆሮንቶስ 9፡6~7) በአዲስ ኪዳን ውስጥ ስለአምልኮ ዓይነት የምናነበው እነዚህን ነው ከእነዚህ ሌላ የተፃፈ የለም ሲለዚህ በነዚህ መወሰን አለብን።

6. የአምልኮ ስብሰባዎችን በታማኝነት እንድንሳተፍ ተነግሮናል

የዕብራዊያን ፀሐፊ እንዲህ ይለናል “በአንዳንዶቹም ዘንድ ልማድ እንደሆነው መሰብሰባችንን አንተው እርስበርሳችን እንመካከር እንጂ ይልቁንም ቀኑ ሲቀርብ እያያችሁ አብልጣችሁ ይህን አድርጉ” (ዕብራዊያን 10፡25)

7. የአምልኮ መንገዱ ቀላል ነው

ለመሳተፍ ለማንም የዳነ ሰው አስቸጋሪ አይደለም ይልቁንም ሁሉም እንዲሳተፉ ተጋብዘዋል

8. ሁሉም የአምልኮ ፕሮግራም በጌታ ቃል ትምህርት ላይ የተመሰረተ ነው

የምንናገረኡ እንደእግዚአብሄር ቃል ነው (1ኛ ጴጥሮስ 4፡11)ጌታ ካለው ውጢ ምንም የሚጨመር የሚቀነስ የለም፡፡ የክርስቶስ ቤተክርስቲያን የምትከተለው በአዲስ ኪዳን ውስጥ የተፃፉትን የአምልኮ ሥርዓት ብቻ ነው፡፡ ስለዚህ እንደሌሎቹ ብዙ የሐይማኖት ድርጅቶች የራሳችንን ሃሳብ አንጨምርም ወይም ያለታዘዘውን አናደርግም፡፡ ለምሣሌ

1. የሙዚቃ መሣሪያ የለንም አንጠቀምም አዲስ ኪዳን በግልፅ እግዚአብሄርን እንዴት ልናመልክ እንደሚገባን ይናገራል እግዚአብሄርን በመዝሙር እንድናመሰኘው ተፅፏል "በመዝሙርና በዝማሬ በምንፈሳዊም ቅኔ እርስበርሳችሁ ተነጋገሩ ለጌታ በልባችሁ ተቀኙና ዘምሩ" (ኤፌሶን 5፡19) ስለዚህ ጉዳይ መዝሙር በሚል ትምህርታችን በሰፊው እናያለን

2. የተዘጋ በድፍን የሆነ የጌታ እራት የለንም፡፡ ይልቁንም ጳውሎስ ሲፅፍ "ሰው ግን እራሱን ይፈትን እንዲሁም ከእንጀራው ይብላ ከፅዋውም ይጠጣ" ይላል (1ኛ ቆሮንቶስ 11፡28)

3. አስራት አንሰበስብም፡፡ ጳውሎስ ሲጽፍ እንደቀናቸው እንጂ ይህን ያህል ያለው ነገር የለም (1ኛ ቆሮንቶስ 16፡2)

4. ገንዘብን ከጌታ ቀን ወይም ከአምልኮ ቀን ውጪ አናዋጣም፡፡ ብዙ የሐይማኖት ቡድኖች በአምልኮ ቀንም ይሁን ከዚያ ውጪ በተሰበሰቡ ቁጥር ለእግዚአብሄር ቤት እያሉ ከህዝብ ይሰበስባሉ፡፡ ይህ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አይደለም በሳምንቱ የመጀመሪያ ቀን ብቻ አዋጡ ነው የተባለው (1ኛ ቆሮንቶስ 16፡2)

5. በአምልኮ ውስጥ የመዘምራን ወይም ልዩ ዘማሪያን ቡድን የሉንም፡፡ ቅዱሳት መጽሐፍት እያንዳንዱ ክርስቲያን መዘመር እንዳለበት ያስተምራሉ፡፡ ስለዚህ እኛ የጉባኤ መዝሙር ብቻ ነው ያለን ጳውሎስ ሲፅፍ "በልሳን ብጸልይ መንፈሴ ይጸልያል አዕምሮዬ ግን ያለፍሬ ነው፡፡ እንግዲህ ምንድነው? በመንፈስ እጸልያለሁ በመንፈስ እዘምራለሁ በአዕምሮም እዘምራለሁ" ይላል (1ኛ ቆሮንቶስ 14፡14~15)

6. እንደ ፋሲካ ገና ወዘተ ያሉ ልዩ የአምልኮ ቀናት ወይም በዓል የለንም ጳውሎስ ለገላቲያ ወንድሞቹን ሲያስጠነቅቅ "ቀንና ወርን ዘመንንም ዓመትንም በጥንቃቄ ትጠብቃላችሁ ምናልባት በከንቱ ለእናንተ ደክሜአለሁ ብዬ እፈራላችዋለሁ" ይላል (ገላቲያ 4፡10~11)

7. የጌታ እራት በየወሩ ወይም በየ3 ወር ወይም በዓመት አንድ ጊዜ አንወስድም፡፡ ነገር ግን በየሣምንቱ የመጀመሪያ ቀን እንወስዳለን

መጽሐፉ ሲናገር የጥንቶቹ ያደረጉት ይህን ነው (የሐዋርያት ሥራ 20፡7) የትኛው ከሣምንቱ የመጀመሪያ ቀን? የትኛው እንደሆነ ማን ሥልጣን ሰጠ? በሁሉም ሣምንታት ውስጥ የመጀመሪያ ቀን አለ እሱም ጌታን ለማምለክ የምንሰበሰብበት እናም ይህን የጌታ እራትም የምንወስድበት የምንጸልይበት ስጦታ የምንሰጥበት የምንዘምርበጥ

8. ጌታን ለማምለክ በምንም ዓይነት ባህል ወግ ውስጥ አናልፍም፡፡ጴጥሮስ ሲናገር "ከአባቶቻችሁ ከወረሳችሁት ክከንቱ ኑሮአችሁ በሚያልፍ ነገር በብር ወይም በወርቅ ሳይሆን ነውርና እድፍ እንደሌለው እንደበግ ደም በክቡር የክርስቶስ ደም እንደተዋጃችሁ ታውቃላችሁ" (1 ጴጥሮስ 1፡18) ጳውሎስ ሲጨምር "እንደክርስቶስ ትምህርት ሳይሆን እንደሰው ወኛ እንደ ዓለማዊ እንደመጀመሪያ ትምህርት ባለ በፍልስፎናና በከንቱም መታለል ማንም እንዳይማርካችሁ ተጠበቁ" (ቆላስያስ 2፡8)

9. የሰዎችን ዶክትሪን እና ትዕዛዝ አንከተልም፡፡ ጳውሎስ ሲፅፍ "ከዓለማዊ ከመጀመሪያ ትምህርት ርቃችሁ ክክርስቶስ ጋር ከሞታችሁ እንደሰው ሥርዓትና ትምህርት አትያዙ አትቅመስ አትንካ ለሚሉት ትእዛዛት በዓለም እንደምትኖሩ ስለምን ትገዛላችሁ? እነዚህ ሁሉ በመደረግ ሊጠፉ ተወስነዋል" (ቆላስያስ 2፡20~22)

10. በአምልኮአችን የብሉይ ኪዳንን ሕግ አንከተልም፡፡ ብዙዎች ወደ ሕግ ይሄዳሉ፡፡ እንደ ሰንበት ፤ አስራት መክፈል፤ የሙዚቃ መሳሪያ መዘመር ወዘተ፡፡ ነገር ግን ይህ የቅዱስ ቃሉን ክፍል አለአግባብ መጠቀም ነው፡፡ ሕጉ ከንግዲህ አስገዳጅ አይደለም (2ኛ ቆሮንቶስ 3፤ ዕብራዊያን 10፡9፤ ዮሐንስ 1፡17)

ስለዚህ እኛ የክርስቶስ ቤተክርስቲያን የምንከተለው አዲስ ኪዳንን ሳንጨምርበት ሳንቀንስ ሌላም ሳንተካ እንጠቀማለን (ዮሐንስ ራዕይ 22፡18~19፤ ገላቲያ 1፡7~9)እሱ ቀጥታ ሰዎችን ወደ መልካም ነገር መልካም ትምህርት የሚመራ ነውና (2 ጢሞቴዎስ 3፡16~17) እሱ እግዚአብሄርን ወደ መምሰል ወደ ህይወትም ያመጣልና (2 ጴጥሮስ 1፡3)

ሰዎች ሁሉ ወደዚህ የአምልኮ ሥርዓት ሲመለሱ እንዲሁም በሐይማኖት ስም የሚናገሩትንና የሚያደርጉትን ሁሉ የኔ ትተው አንድነት ሊኖረን ይችላል፡፡ በእውነት ጌታ በአንድ መንገድ እኔን ሌላውን በሌላ መንገድ እንዲገዙ እንዲያመልኩት አላዘዘንም ይልቁንም ሁላችንም በአንድነት እንድንሰግድ ይፈልጋል፡፡ እርሱ የሰጠንን አንድ እውነተኛ ምሣሌ መጽሐፍ ቅዱስን ስንከተል ሁላችንም በአንድነት እናመልካለን፡፡

## ጥያቄዎች

1. ለምንድነው የተለያዩ የአምልኮ ሥርዓቶች የተፈጠሩት?

2. በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለስንት ቤተክርስቲያን እናነባለን?
3. ቤተክርስቲያን የማን ናት?
4. የቤተክርስቲያን ሥርዓትን ዬት እናገኛለን?
5. የአምልኮ ሥርዓት ምን ሊሆን ይችላል?
6. መመለክ ያለበት ማን ነው?
7. የአምልኮ ቀን ዬትኛው እንደሆነ ተናገር
8. ጌታን ማምለክ ያለበት ማን እንደሆነ ተናገር
9. እንዴት ነው ማምለክ ያለብን?
10. አምስቱን የአምልኮ ሥርዓቶችን ጥቀስ
11. ለምንድነው የሙዚቃ መሣሪያ የማንጠቀመው?
12. የተዘጋ ጌታ እራት ምንድነው?
13. ምን ያህል ነው መሰብሰብ ያለብን?
14. በአምልኮ ውስጥ በመዘምራን ቡድን ማምለክ ስህተቱ ምንድነው?
15. ለምንድነው ልዩ ቀን እንደ ፋሲካ ገና የማናመልከው?
16. ክርስቲያኖች የጌታ እራትን እንዴት ይወስዳሉ?
17. የሰዎች ትዕዛዝ እና ዶክትሪን ምንድናቸው?
18. የእግዚአብሄር ህዝብ አሁንም ብሉይ ኪዳንን ይከተላሉ?
19. የአዲስ ኪዳን ከምን ጋር ይስተናገዳል?
20. በሐይማኖት ውስጥ አንድነት እንዲኖር ማድረግ ይቻላል? ከተቻለ እንዴት ?

## ትምህርት ስምንት
## የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት

በአዲስ ኪዳን ጌታን ስናመልክ ከምንፈፅማቸው ነገሮች ውስጥ አንዱ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ነው። ይህንን ስለታዘዝን ብቻ የምናደርገው ሳይሆን የጥንቶቹ ክርስቲያኖችም ለአምልኮ ሲሰበሰቡ የድረጉት ነበርና ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ ጥናት በማንኛውም ጊዜ በአንድ ግለሰብ ወይም ከዚያ በላይ ሊካሄድ ይችላል። ነገር ግን እዚህ ላይ የምናስበው በሣምንቱ የመጀመሪያ ቀን የአምልኮ ሥርዓቱ አካል ሆኖ መካፈል ነው። በዚህም ጌታ በቃሉ ይናገረናል።

ይህ የአምልኮ ክፍል ቅዱሳት መጻሕፍትን በማንበብና በማጥናት ወይም አንድ ሰው ከእግዚአብሄር ቃል ሲሰበክ በመስማት ሊገባ ይችላል። በሐዋሪያት ሥራ 20፡7 ላይ ጳውሎስ ለአምልኮ በተሰበሰቡበት ወቅት ወንድሞችን ሲሰብካቸው እናያለን ሌላ የምናነበው ድግሞ “ ወዲያውም ወንድሞች ጳውሎስንና ሲላስን በሌሊት ወደ ቤሪያ ሰደዷቸው በደረሱም ጊዜ ወደ አይሁድ ምኩራብ ገቡ እነዚህም በተሰሎንቄ ከምኖሩት ይልቅ ልበ

ሰፊዎቹ ነበሩና ነገሩ እንዲዚሁ ይሆንን? ብለው ዕለት ዕለት መጻሕፍትን እየመረመሩ ቃሉን በሙሉ ፈቃድ ተቀበሉ። ስለዚህም ከእነርሱ ብዙ ከግሪኮቹም የከበሩት ሴቶቹና ወንዶች ጥቂት ያይደሉ አመኑ" (የሐዋሪያት ሥራ 17፡10~12)፤ ክርስቶስም ሲያስተምር " እናንተ በመጻሕፍት የዘላለም ህይወት እንዳላችሁ ይመስላችሁዋልና እነሱን ትመረምራላችሁ እነርሱም ስለእኔ የሚመሰክሩ ናቸው" (ዮሐንስ 5፡39) ጳውሎስ ወጣቱን ወንጌላዊ ሲመክር "የእውነትን ቃል ብቅንነት የሚናገር የማያሳፍርም ሠራተኛ ሆነህ የተፈተነውን ራስህን ለእግዚአብሄር ልታቀርብ ትጋ" (2ኛ ጢሞቴዎስ 2፡15) ክርስቶስ ሲናገር "ፅድቅን የሚራቡና የሚጠሙ ብፁዓን ናቸው ይጠግባሉና" (ማቴዎስ 5፡6) እንዷገናም "ሰው ከግዚአብሄር ቃል በሚወጣ ቃል ሁሉ እንጂ በእንጀራ ብቻ አይኖርም ተብሎ ተፅፏል" አለ (ማቴዎስ 4፡4)

ማጥናት ብቻ ሳይሆን ትክክለኛውን ነገር ማጥናታችን በጣም አስፈላጊ ነው። የምንሰማው ስብከት ወይም ትምህርት እንዲሁ ነው ። ሐአዋሪያው ጳውሎስ "እንግዲያውስ እምነት ከመስማት ነው መስማትም በእግዚአብሄር ቃል ነው" (ሮሜ 10፡17)። ይህ ማለት የሰማነው ስህተት ከሆነ የምናምነውም ስህተት ይሆናል ማለት ነው። በተለይ የምንሰማውን የማንመረምር ከሆነ። ነገር ግን  እውነትን ከሰማን በትክክል ያንን እውነት ወደ ማመን እንመጣለን።

እግዚአብሄር ዛሬ ይናገረናል የሚናገረንም በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ነው። (ዕብራዊያን 1፡1~2) በተራራው ላይ በተገለጠው ጊዜ ኢየሱስን በተመለከተ የተሰማው ድምፅ "እርሱም ገና ሲናገር ብሩህ ደመና ጋረዳቸው እነሆም ከደመናው ፦ በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው እርሱን ስሙት የሚል ድምፅ መጣ" (ማቴዎስ 17፡5) ክርስቶስ የእግዚአብሄርን ቃል ተናግሮአል "የሚወደኝ ቢኖር ቃሌን ይጠብቃል አባቴም ይወደዋል ወደ እርሱም እንመጣለን በርሱም ዘንድ መኖሪያ እናደርጋለን። የማይወደኝ ቃሌን አይጠብቅም የምሰሙትም ቃል የላከኝ የአብ ነው እንጂ የእኔ አይደለም" አለ (ዮሐአንስ 14፡23~24) ከዚያም ይህ ቃል ተዘግቦአል "ኢየሱስም በዚህ መጽሐፍ ያልተጻፈ ሌላ ብዙ ምልክት በደቀመዛሙርቱ ፊት አደረገ። ነገር ግን ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ የእግዚአብሄር ልጅ እንደሆነ ታምኑ ዘንድ አምናችሁም በስሙ ህይወት ይሆንላችሁ ዘንድ ይህ ተጽፏል" አለ (ዮሐንስ 20፡30~31) በአጠቃላይ ሁሉም የእግዚአብሄር ቃል በመንፈስ ቅዱስ ምሪት የተጻፉ ሲሆን እነሱም ወደ መላክም ነገሮችህ ሁሉ ለማቅናት ነው። (2 ጢሞቴዎስ 3፡`16~17፤ ያዕቆብ 1፡25)።

ከላይ የተገለፀው እውነት ሆኖ ሳለ የእግዚአብሄርን ቃል ለማጥናት ብጌታ ቀን የምንሰበሰብበት ብዙ ምክንያቶች አሉን

1. የእግዚአብሄር ቃል ነውና ልናደርገው ይገባል (ዕብራዊያን 13፡7፤

1 ጴጥሮስ 1፡23፣ ኤፌሶን 6፡17) ጌታ በጨለማ ውስጥ ሳይተወን ፈቃዱን መገለጡ እንዴት ድንቅ ነው።

2. የእግዚአብሄርን ፈቃድ በበለጠ ማወቅ እንፈልጋለን (ሐአዋሪያ 13፡7)። ስለዚህ ለመማር ማጥናት የኛ ፋንታ ነው። ጌታ አስተዋይ አዕምሮ ሰጥቶናል እናም ሁላችንም ማንበብ እና ማጥናት እንችላለን ለራሳችን የጌታን ፈቃድ ለማወቅ።

3. እንዳንታለል ማጥናት እንፈልጋለን (ኤፌሶን 5፡6፤ ኤፌሶን 4፡14፤ ያዕቆብ 1፡22) ብዙ በክርስትና ስም የሚያስተምሩ አሉ። ነገር ግን እውነት መሆኑን ወይም አለመሆኑን እንዴት ማወቅ እንችላለን ? የምንሰማውን ከእግዚአብሄር ቃል ጋር በማነፃፀር ነው። ዮሐንስ መናፍስትን ወይም ሰባኪዎችን ከአምላክ እንደሆኑ ወይም እንዳልሆኑ ለማወቅ እንድንሞክር አሳስቧል (1ኛ ዮሐንስ 4፡1) ማንም ሰው የአምላክን ቃል መመርመሩን እስካልቀጠለ ድረስ መታለሉ አይቀርም።

4. የእግዚአብሄርን ቃል የምናጠናው ተምረን እኛም ሌሎችን እንድናስተምር ነው። ጳውሎስ ሲናገር “ለራስህና ለትምህርትህ ተጠንቀቅ በእነዚህም ፅና ይህን ብታደርግ ራስህንም የሚሰሙህንም ታድናለህና “ (1 ጢሞቴዎስ 4፡16) ክርስቲያኖችን በተመለከተ ዘገባው እንደሚል “የተበተኑትም ቃሉን እየሰበኩ ዞሩ” ይላል (የሐዋርያት ሥራ 8፡4)።

በጥናታችን በመቀጠል ወደ ጢሞቴዎስ 2፡15፣ እንድንመለስ እወዳለሁ። ጳውሎስ የእውነትን ቃል በትክክል ለመከፋፈል ማጥናት እንዳለብን ተናግሯል። አሁን በትምህርታችን ይህንን ማድረግ መማር አለብን። ማለትም መጽሐፍ ቅዱስ በብሉይ ኪዳን እና አዲስ ኪዳን የተከፋፈለ ሆኖ እናገኘዋለን። ብሉይ ኪዳን የአባቶችን እና የሙሴ ሕግጋቶችን እንደያዘ እንማራለን። ሁለቱም ካሁን በኃላ አስገዳጅ አይደሉም እና አዲሱ ኪዳን የክርስቶስን ሕግ ይዟል። ስለዚህ አንዱ ያረጀ አንዱም አዲስ ነው። ኝ እኛ ዬት ነን? እኛ የምንኖረው በዚህ የመስቀል ክፍል ላይ እንደመሆናችን መጠን በአዲስ ኪዳን እንደተዘገበው ከክርስቶስ ሕግ በታች እንኖራለን (ዕብራዊያን 9፡16~17፣ ዕብራዊያን 10፡9)

እንግዲህ ጥያቄው የሚመጣው አሮጌውን ኪዳን የእግዚአብሄር ቃል ነው? ለሚለው በእርግጠኝነት መልሱ አዎን ነው። ሆኖም እንደሕግ በእኛም ሆነ በማንም ላይ አስገዳጅነት የለውም። ታዲያ ብሉይ ኪዳንን ለምን እናጠናለን? በብዙ ምክያቶች እናጠናለን

1. ስለፍጥረትና ስለነገሮች ለማወቅ እናጠናለን

2. የሰውን ታሪክ እና እግዚአብሄር ከሰው ጋር ምን እንዳደረገ ለማወቅ እናጠናለን

3. ምክን ያቱም ጳውሎስ የተጻፈው ለእኛ ምሣሌ ነው ብሏል (1ኛ ቆሮንቶስ 10፡6) እንደእውነቱ ከሆነ ብዙ ምሣሌዎችን ይዟል።

4. በውስጡ ብዙ መርሆች ስላሉ ሲሰጡ እንደነበረው ዛሬም

እውነት የሆኑ ነገር ግን ከሕግ ጋር ምንም ግንኙነት የሌላቸው።

5. የሚሻል ሕግ ሥር እንድንኖር የሚበልጥም ተስፋ እንዲኖረን እናያለን (ዮሐንስ 1፡17)

አሁን የእግዚአብሄር ቃል በብቃት እንድናጠና እና ቃሉን በትክክል እንድንከፋፈል እንዲረዳን እንግዲያውስ ለመጽሐፍ ቅዱስ አንዳንድ ደንቦች እዚህ አሉ።

1. ፅሑፉን ብዙ ጊዜ አንብብ
2. እንዲሁም አውዱን አንብብ
3. ተናጋሪ ማን ነው?
4. ለማን ነው የሚናገረው?
5. መቼ ነው የተነገረው?
6. ምሣሌያዊ ነው ወይስ ቀጥተኛ ቋንቋ ?
7. ትዕዛዝ ነው?
8. መዳናችንን ይመለከታል?

እብዲሁም እነዚህ መሣሪያዎች በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናትዎ ላይ ሊረዱዎት ይችላሉ። የተለየ ትርጉም የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት የመጽሐፍ ቅዱስ ኮንኮርዳንስ ሐተታ ወዘተ። ነገር ግን ከሁሉም በላይ መጽሐፍ ቅዱስን በጸሎት አጥና አንብብ። ብዙ ሰዎች ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ያውቃሉ ነገር ግን በውስጡ የያዘውን ጥቂት ያውቃሉ።

እኔ እና አንተ ጌታ እንደጠየቀን ስናደርግ እና በየሣምንቱ የመጀመሪያ ቀን ከቅዱሳን ጋር ተሰብስበን ስናጠና ያን ጊዜ እንደክርስቲያን እንድናድግና እንድንጠነክር የሚረዳን የመጽሐፍ ቅዱስ ዕውቀት እናገኛለን ። ሁሉም ይህን ቢያደርግ ቤተክርስቲያን የበለጠ ጠንካራ ትሆናለጭ እና ምናልባትም የሚያድነን የሚለውጠን የእግዚአብሄር ቃል እንደሆነ የሃይማኖት ጓደኞቻችንን ልናሳምን እንችላለን።

## ጥያቄዎች

1. በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ውስጥ ማን ሊሳተፍ ይችላል?
2. የጌታን ቃል የምንሰማው እንዴት ነው?
3. የቤሪያ ስዎች ከተሰሎንቄ ሰዎች የበለጠ የታወቁበት በምንድነው?
4. ኢየሱስ በ ዮሐንስ 5፡39 ላይ ምን አለ?
5. 2 ጢሞቴዎስ 2፡15 ጥቀስ
6. እነማንን ነው ክርስቶስ ብሩካን ናቸው ይጠግባሉና ያላቸው?
7. ሰው በእንጀራ ብቻ ሊኖር ይችላል?
8. እምነት እንዴት ይመጣል?
9. እኛ ስህተተ ከሰማን የሚሆነው ምንድነው?
10. እግዚአብሄር ለሰው የሚናገረው በምን በኩል ነው?

11. የኢየሱስ ትምህርቶች ለምን ተጻፉ?
12. 2ኛ ጢሞቴዎስ 3፡16~17፣ እና ያዕቆብ 1፡25 ጥቀስ
13. ስንሰበሰብ ቃል የምናጠናበትን ጥቂት ምክንያት ጥቀስ
14. ቃሉን በትክክል መከፋፈል ማለት ምን ማለት ነው?
15. ሦስቱን የተዘገቡ ሕጎች ጥቀሳቸው
16. እኛ በዬትኛው ሕግ ሥር ነን?
17. የብሉይ ኪዳን የእግዚአብሄር ቃል ነው?
18. ብሉይ ኪዳንን የምናጠናው ለምንድነው?
19. መጽሐፍ ቅዱስን ስናነብ መከተል ያለብንን መርሆች ጥቀሳቸው
20. ሌሎች መጽሐፍ ቅዱስ ማጥኛ መሳሪያዎች ምንድናቸው
21. የመጽሐፍ ቅዱስ ዕውቀት እንዴት ነው የሚረዳን?

## ትምህርት ዘጠኝ
## ፀሎት

ሌላው በአምልኮ ላይ ከሚፈፀሙ ውስጥ አንዱ ፀሎት ነው። የጥንቶቹ ክርስቲያኖች ቤተክርስቲያን እንደተመሰረተች ተሰብስበው በአምልኮ ካደረጉት ውስጥ አንድ ፀሎት ነበር። ዘገባው እንዲህ ይላል "በሐዋሪያትም ትምህርትና በኅብረት እንጀራውንም በመቁረስ በየፅሎቱም ይተጉ ነበር" (የሐዋሪያት ሥራ 2፡42) "በየፀሎቱም" ይህ በዚህ የአምልኮው ክፍል ላይ የተሰጠውን ትኩረት የሚያመለክት ነው።

ፀሎት የሚለው ቃል ምልጃ፣ አማላጅነት፣ ልመና፣ ወይም በቀላሉ ጌታን የመናገር ወይም የማናገር ማለት ነው። የአምልኳችን አካል ብቻ ሳይሆን የዕለት ተዕለት ህይወታችን አካል መሆንም ጭምር ነው። ጳውሎስ ሲፅፍ እንዲህ ይላል "በፀሎትና በልመናም ሁሉ ዘወትር በመንፈስ ፀልዩ በዚህም አሳብ ስለቅዱሳን ሁሉ እየለመናችሁ በመፅናት ሁሉ ትጉ" (ኤፌሶን 6፡18) እንደገናም "ሳታቋርጡ ፀልዩ በሁሉ አመስግኑ" (1ኛ ተሰሎንቄ 5፡17) ይህ በቀላሉ አንድ ክርስቲያን ሁልጊዜ የፀሎት መንፈስ ሊኖረው እንደሚገባው ነው።

ይህንን ሁሉ አስፈላጊ ርዕሰ ጉዳይ ስንመለከት አንዳንድ ዋና ዋና ነጥቦችን እንዘርዝር

1. ፀሎት በዋነኛነት ለክርስቲያኖች ወይም ለእግዚአብሄር ልጆች የተጠበቀ ነው።

ይህ ማለት ክርስቲያን ያልሆነ ሰው መፀለይ የለበትም ማለት አይደለም ነገር ግን ቅዱሳት መጽሕፍት ፀሎት የክርስቲያን መብትና በረከት እንደሆነ ያስረዳሉ እንዲህም እናነባለን "እግዚአብሄርን የሚፈራ ፈቃዱንም የሚያደርግቢኖርር ያንን እግዚአብሄር ይሰመዋል እንጂ ኃጥያተኞችን እንዳይሰማ እናውቃለን" (ዮሐንስ 9፡31)፡፡፣ አሁን ጌታ

ፀሎትን እንዲሰማ የተነገሩትን ሁኔታዎች የሚመለከተው የእግዚአብሄር አምላኪ እና ፈቃዱን የሚያደርግ መሆን አለበጥ ማን ነው ይሄ? በርግጥ ክርስቲያን ነው። ኃጥያተኛ ስለምን ሊፀልይ ይችላል? ጌታ ኃጥያቱን ይቅር እንዲለው መፀለይ አይችልም ምክን ያቱም የኃጥያት ሥርዬት ሊገኝ የሚችልበትን ክርስቶስ ተናግሮአልና ያመነ የተጠመቀም ይድናል (ማርቆስ 16፡16)፣ ስለ እምነትም ሊፀልይ አይችልም ምክንያቱም ቅዱሳት መጽሀፍት እምነት ከመስማት  እና ይህ መስማት ደግሞ ወደድ መድሃን እንደሚያደርስ ይናገራልና (ዮሐንስ 20፡30፤1፣ ሮሜ 10፡17) እንደ ኃጥያተኛ ሌላ ነገር ከመፀልይ ውጪ በዚህ ጉዳይ መፀለይ አይችልም።

በአዲስ ኪዳን ውስጥ ስናይ እና ስለ ፀሎት የሚናገሩትን ብዙ የቅዱሳት መጽሀፍት ምንባቦችን ስናነብ ሁሉም ወደ ክርስቲያን እንደሚሄዱ እናስተውላለን። ክርስቲያን በመታዘዝ የእግዚአብሄር ልጅ ነው። (ገላቲያ 3፡26~27) አባ አባት ብለው የሚጠሩበትን መብት አላቸው (ሮሜ 8፡15) ታዲያ ኃጥያተኞችም ቅዱሳንም በፀሎት ውስጥ አባት ብለው የሚጠሩ ከሆነ እና የሚሰማቸው ከሆነ ቅዱሳን ከኃጥያተኛ በተሻለ ምን ጥቅም ያገኛል ? ስለዚህ ክርስቲያን የተለየ የፀሎት መብት እንዳለው እና ይህም ክርስቲያን በመሆን የሚያገኘው ከመንፈሳዊ በረከቶች አንዱ መሆኑን በእርግጠኝነት ማየት ትችላለህ (ኤፌሶን 1፡3)።

ዛሬ ኃጥያተኛው ለኃጥያቱ ሥርየት መፀለይ እና በዚህም ክርስቲያን የመሆኑን ሰፊ ልምድ አለን። ነገር ግን ይህ በእግዚአብሄር ቃል የተደገፈ ሳይሆን የሰዎች ትምህርት ነው።

2. ፀሎታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ወደ እግዚአብሄር መቅረብ አለበት

እግዚአብሄር አባት ነው እናም ሁሉንም በረከቶች ሰጪ እሱ ነው። እሱ እንዲረዳን መጥራታችን ትክክል ነው። ነገር ግን ኃጥያት በመካከላችን ስለገባ በቀጥታ ወደ እግዚአብሄር መቅረብ አንችልም። በአንጻሩ ያ ማለት በህይወት ውስጥ ያለው ደረጃ ምንም ይሁን ምን ስለእኛ ሊማልድ ወደ አንድ ሰው መመልከት አለብን ማለት አይደለም። ይልቁንም ኢየሱስ አስታራቂያችን አማላጃችን ነው። በርሱም ወደ ጸጋው ዙፋን የምንቀርብበት የእግዚአብሄርን ቃል እንስማ “ልጆቼ ሆይ ኃጥያት እንዳታደርጉ ይህን እጽፍላቸዋለሁ። ማንም ኃጥያትን ቢያደርግ ከአብ ዘንድ ጠበቃ አለን እርሱም ጻድቅ የሆነ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው እርሱም የኃጥያታችን ማስተሰሪያ ነው።ለኃጥያታችን ብቻ አይደለም ነገር ግን ለዓለሙ ሁሉ ኃጥያት እንጂ” (1ኛ ዮሐንስ 2፡1~2)  “አንድ እግዚአብሄር አለና በእግዚአብሄርና በሰው መካከል ያለው መካከለኛው ደግሞ አንድ አለ እርሱም ሰው የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው” (1ጋን ጢሞቴዎስ 2፡5) ስለዚህ ሁልጊዜ ስንፀልይ በኢየሱስ ስም ወይም በስሙ ሥልጣን መጸለይ አለብን (ማቴዎስ 28፡18)።

3. በመንፈስና በእውነት መፀለይ አለብን

በባለፈው ትምህርታችን ጌታ በመንፈስና በእውነት እግዚአብሄርን ማምለክ እንዳለብን ነግሮናል (ዮሐንስ 4፡24) ፀሎት የአምልኮ አካል እስከሆነ ድረስ እንዲሁም የክርስቲያኖች የዕለት ዕለት ህይወት እስከሆነ ድረስ ፀሎታችንም በመንፈስና በእውነት መሆን አለበት ።ጳውሎስ ለቆርንቶስ ክርስቲያኖች ሲፅፍ “በልሣን ብፀልይ መንፈሴ ይፀልያል አዕምሮዬ ግን ያለ ፍሬ ነው። እንግዲህ ምንድነው? በመንፈስ እፀልያለሁ በአዕምሮም ደግሞ እፀልያለሁ በመንፈስ እዘምራለሁ በአዕምሮም ደግሞ እዘምራለሁ” ይላል (1ኛ ቆሮንቶስ 14፡14~15) ይሄ ማለት ጸሎታችን ከማስተዋል ጋር መሆን አለበት፤ አዕምሯችን በምንናገረው ነገር ላይ ይሁን እና በእነርሱ ትሁትና ቅን መሆን አለብን። በተጨማሪም ፀሎታችን ከቅዱሳት መጽሀፍት ጋር የሚስማማ መሆን አለበጥ ጌታን ከፈቃዱ ተቃራኒ የሆነውን እንዲያደርግ ልንጠይቀው አይገባንም ማለት ነው። ክርስቶስ በአንድ ወቅት አንዳንድ ደቀመዛሙርት የሞኝነት ጥያቄ ባቀረቡበት ጊዜ የተናገረው “የምትለኑትን አታውቁም። እኔ ልጠጣው ያለውን ፅዋ ልትጠጡ እኔም የምጠመቀውን ጥምቀት ልትጠመቁ ትችላላችሁን? አለ” (ማቴዎስ 20፡22) እንደገናም “ጌታ አምላክህን አትፈታተነው ተብሎ ተፅፎአል አለው” (ማቴዎስ 4፡7)

“የጌታ ፀሎት” የተባለውን መጠቀም ከማንችልበት አንዱ ምክንያት ይህ ነው። (ማቴዎስ 6፡9~13)አሁን መንግስቱ እንድትመጣ እንድንፀልይ ከጌታ ፈቃድ ጋር አይስማማም መጥታለችና (ዕብራዊያን 12፡28)

4. የፀሎታችን ይዘት በቅዱሳት መጻህፍት ውስጥ በግልጽ ተቀምጧል።

የምስጋና ፀሎት መፀለይ አለብን “ጌታ ቅርብ ነው። በነገር ሁሉ በፀሎትና በምልጃ ከምስጋና ጋር በእግዚአብሄር ዘንድ ልመናችሁን አስታውቁ እንጂ በአንዳች አትጨነቁ” (ፊልጵስዩስ 4፡6)

በጣም አስፈላጊ ለሆነው ጉዳይ መፀለይ አለብን “ጴጥሮስም በወይኒ ይጠበቅ ነበር ነገር ግን በቤተክርስቲያን ስለእርሱ ወደ እግዚአብሄር ጸሎት አጥብቆ ይደረግ ነበር” (ሐዋሪያት ሥራ 12፡5)

ለሀገር መሪዎች መጸለይ አለብን (ሮሜ 13)

ለእርስበርሳችን መጸለይ አለብን “እርስ በርሳችሁ በኃጥያታችሁ ተናዘዙ ትፈወሱም ዘንድ እያንዳንዳችሁ ስለ ሌላው ይፀልይ የጻድቅ ሰው ጸሎት በሥራዋ እጅግ ኃይል ታደርጋለች” ያዕቆብ 5፡16)

ለታመሙት መጸለይ አለብን “ከእናንተ የታመመ ማንም ቢኖር የቤተክርስቲያን ሽማግሌዎችን ወደ እርሱ ይጥራ በጌታም ስም እርሱን ዘይት ቀብተው ይፀልዩለት የእምነትም ጸሎት ድዉዩን ያድናል። ጌታም ያስነሣዋል ኃጥያትንም ሠርቶ እንደሆነ ይሰረይለታል” (ያዕቆብ 5፡14~15)

እናም በመቀጠል ልንጸልይላቸው ስለሚገቡ የተለያዩ ነገሮች እና

ግለሰቦች የሚናገሩትን ብዙ የቅዱሳት መጻህፍት ጥቅሶችን መዘርዘር እንችላለን። ይህም ቤተክርስቲያንን፣ የጠፉትን ቤተሰቦቻችንን እና የመሳሰሉትን ይጨምራል።

5. ቅዱሳት መጻህፍት ስለ ፀሎት አንዳንድ ማስጠንቀቂያዎችን ይሰጣሉ

ክርስቶስ ሲናገር እንዲህ ይላል "ስትፀልዩም እንደግብዞች አትሁኑ ለሰው ይታዩ ዘንድ ብምኩራብና በመንገድ ማዕዘን ቆመው መጸለይን ይወዳሉና እውነት እላችዋለሁ ዋጋቸውን ተቀብለዋል። አንተ ግን ስትፀልይ ወደ እልፍኝህ ግባ መዝጊያህንም ዘግተህ በስውር ላለው አባትህ ፀልይ በስውር የሚያይ አባትህም በግልጥ ይከፍልሃል። አህዛብም በመናገራቸው ብዛት እንዲሰሙ ይመስላቸዋልና ስትፀልዩ እንደነርሱ በከንቱ አትድገሙ ስለዚህ አትምሰሏቸው ሳትለምኑት አባታችሁ የሚያስፈልጋችሁን ያውቃልና" (ማቴዎስ 6፡5~8) እንደገናም "ለሰዎች ኃጥያታቸውን ይቅር ብትሉ የሰማዩ አባታችሁ ደግሞ ይቅር ይላችዋልና ልሰዎች ግን ኃጥያታቸውን ይቅር ባትሉ አባታችውም ኃጥያታችውን ይቅር አይላችውም" (ማቴዎስ 6፡ 14~15)

ስለዚህ ጸሎት እንደ የአምልኮ አገልግሎታችንም ሆነ የዕለት ተዕለት ህይወታችን አንድ አካል ስንቆጥረው ጸሎት ትልቅ ርዕሰ ጉዳይ ነው። እንደክርስቲያን ግን በሁለቱም አጋጣሚዎች እግዚአብሄርን የመጥራት መብት አለን። ይህ ብቻ ሳይሆን ጌታም ከኛ የሚጠብቀው ነው።አምልኮን በሚመለከት ግን ክርስቲያኖች በቤት ውስጥ ከመቆየት እና ገንዘባቸውን ከመስጠት ወይም የጌታ እራት መካፈልን ወደ ቤተክርስቲያን ስብሰባ መገኘት አለባቸሀው። ለአምልኮ የሚሰበሰቡ ክርስቲያኖች እቤታቸውም ይፀልያሉ። ነገር ግን ለአምልኮ የማይሰበሰቡ ክርስቲያኖች እቤትም የማይጸልዩ ናቸው ቢያደርጉም ለጌታ ታማኝ መሆንን እስኪማሩ ድረስ ምንም ፋይዳ የለውም።

በእምነት ፀልዩ~~~~ጠይቁ እናም ትቀበላላችሁ ፀሎት ኃይል አለው።

## ጥያቄዎች

1. ፀሎት የሚለውን ቃል አብራራ
2. በህይወታችን ልንጫወት የሚገባን ሚና ምንድነው?
3. ምን ያህል ነው መጸለይ የሚገባን?
4. ጸሎት የማን መብት ነው?
5. ዮሐንስ 9፡31 አንብብና ግለጽ
6. ኃጥያተኛ ስለምን ይጸልያል?
7. ክርስቲያን ማን ነው?
8. ለእግዚአብሄር በጸሎት የሚቀርበው ማን ነው?
9. ኃጥያተኛ በጸሎት መዳን ይችላል?

10. በማን በኩል ነው ወደ እግዚአብሄር የምንጸለየው?
11. ኢየሱስ ለእኛ ምናቸን ሆኖ ነው?
12. በመንፈስና በእውነት መጸለይ ምን ማለት እንደሆነ ግለጽ
13. ለእኛ በጸሎት እግዚአብሄርን መፈታተን እንችላለን?
14. "የክርስቶስ ጸሎት" ምን ማለት ነው?
15. ይህን ጸሎት የማንጠቀመው ለምንድነው?
16. ልንጸልይባቸው የሚገቡንን ነገሮች ጥቀሳቸው
17. እነማን ናቸው የምንጸልይላቸው?
18. ጌታ ስለ ጸሎት ያስጠነቀቃቸውን ጥቀሳቸው
19. ክርስቲያኖች ለአምልኮ ስብሰባ ላይ ሳይገኙ እቤታቸው መጸለይ ይችላሉ?
20. እንዴት ነው የምንጸልየው?

## ትምህርት አሥር
## መዘመር

የክርስትና ሐይማኖት የመዘመር ሐይማኖት ነው፡፡መዘመር አንድ በአምልኮ ላይ ሊፈጸም የሚገባው በአዲስ ኪዳን ውስጥ ከተዘገበው የጌታ ቃል ነው፡፡ በዚህ በጣም አስፈላጊ የአምልኮ ክፍል ጥናታችን ላይ ጊዜ ወስደን እናያለን

ከሁሉም በፊት ከዚህ ርዕስ ጋር የሚስማማውን ጥቅሶች ከቅዱሳት መጽህፍት እንመለከታለን

1 "መዝሙርም ከዘመሩ በኃላ ወደ ደብረ ዘይት ወጡ" (ማቴዎስ 26፡ 30)

2 "በመንፈቀ ሌሊት ግን ጳውሎስና ሲላስ እየፀለዩ እግዚአብሄርን በዜማ ያመሰኑ ነበረ እስረኞችም ያደምጧቸው ነበር" (የሐአዋሪያት ሥራ 16፡25)

3 "ደግሞም ስለዚህ በአህዛብ መካከል አመሰግንሃለሁ ለስምህም እዘምራለሁ ተብሎ እንደተጻፈ አህዛብ ስለ ምህረቱ እግዚአብሄርን ያከብሩ ዘንድ ክርስቶስ ስለ እግዚአብሄር እውነት የመገረዝ አገልጋይ ሆነ እላለሁ" (ሮሜ 15፡9)

4 " እንግዲህ ምንድነው በመንፈስ እዘምራለሁ በአዕምሮም ደግሞ እዘምራለሁ" (1ኛ ቆሮንቶስ 14፡15)

5 "በመዝሙርና በዝማሬ በመንፈሳዊ ቅኔ እርስበርሳችሁ ተነጋገሩ ለጌታ በልባችሁ ተቌኙና ዘምሩ" (ኤፌሶን 5፡19)

6. "የእግዚአብሄር ቃል በሙላት ይኑርባችሁ በጥበብ ሁሉ እርስበርሳችሁ አስተምሩና ገስፁ በመዝሙርና በዝማሬ በመንፈሳዊም ቅኔ በጸጋው በልባቸው ለእግዚአብሄር ዘምሩ" (ቆላስያስ 3፡16)

7. "ስለዚህም ስምህን ለወንድሞቹ እነግራቸዋለሁ በማህበርም

መካከል በዜማ አመሰግንሃለሁ" (ዕብራዊያን 2፡13)

8. "ከእናንተ መከራን የሚቀበል ማንም ቢኖር እርሱ ይፀልይ ደስ የሚለውም ማንም ቢኖር እርሱ ይዘምር" (ያዕቆብ 5፡13)

9. " አዲስን ቅኔ ይዘምራሉ" (ዮሐንስ ራዕይ 5፡11)

10. "በዙፋኑም ፊት በአራቱም እንስሶችና በሽማግሌዎች ፊት አዲስ ቅኔ ዘመሩ" (ዮሐንስ ራዕይ 14፡3)

11. የእግዚአብሄርን ባሪያ የሙሴን ቅኔና የበጉን ቅኔ ይዘምራሉ" (ዮሐንስ ራዕይ 15፡3)

በአዲስ ኪዳን ገፆች በሙሉ መዝሙርን በተመለከተ የተጻፉት ጥቅሶች እነዚሁ ብቻ ናቸው፡፡ በዚህ ረገድ ጌታ የሚፈልገው ምን እንደሆነ ግልፅ ሆኖ ይታያል፡፡ የበለጠ ወይም ያነሰ ነገር ከቃሉ ጋር የሚስማማ አይሆንም፡፡፤

አብዛኞቹ ሐይማኖተኛ ሰዎች በሙዚቃ መሣሪያ መዘመርን ይጠቁማሉ ይህንም የመካኒካል ሙዚቃን ይጠቀማሉ፡፡ስለዚህ እነዚህ ሰዎች ከዘፈናቸው ጋር የሚሄድን ሙዚቃ አላቸው፡፡ ነገር ግን አዲስ ኪዳን ባአምልኮ አገልግሎታችን ውስጥ መዝሙር ሊኖረን እንደሚገባ እንደሚያስተምር ሁሉም ቢስማሙም በመካኒካል ሙዚቃ መዘመርን ሁሉም አይስማሙም፡፡ ግን መጽሃፍ ቅዱስ ምን ይላል? መዘመርን ብቻ ያስተምራል ወይንስ መካኒካል ሙዚቃ ለአምልኮ መጠቀም አለበት ይላል? ያለ መካኒካል ሙዚቃ መዘመር ይቻላል? ከመካኒካል ሙዚቃ ማምለክ ይቻላል? ሁለቱንም ማድረኝ ነው? እስቲ ቃሉ የሚለውን እንይ

በመጀመሪያ ደረጃ በሰው ዘንድ የሚታወቁ ሁለት ዓይነት ሙዚቃዎች እንዳሉ እናስተውላለን፡፡ ድምፃዊ እና መካኒካል፡፡ ድምፅ የሚመረተው በሰው ልጅ የድምፅ አውታር ነው፡፡ ስለዚህ ከግለሰብ ውስጥ ይወጣል ህያው ነው ከእግዚአብሄር ፍጥረት የተገኘ ነው፡፡ ስለዚህ በዓለም ላይ ካሉት እጅግ በጣም ቆንጆ ሙዚቃዎች የሚመጡት ከሰው ድምፅ የሚመጡ ድምፆችን በማጣመር ነ ተብሏል፡፡ መካኒካል ሙዚቃ በተቃራኒው ነው በሰው የተሠራ ነው ቀዝቃዛ ነው፡፡ መንፈስ የለውም ልብ የለውም ህይወት የለውም፡፡ ድምፆቹን የሚያሰማበት ብቸኛው መንገድ አንድ ሰው ሲመታው ነው፡፡ ገመዶቹን ስለሚመታ ወይም በሱ ውስጥ ያለውን ሲነካካ እና እንደ መሣሪያው ዓይነት ሲሆን የስው እገዛ ብቻ ድምጽ ይሆናል፡፡ ይህ የእግዚአብሄር ድርጊት ሳይሆን ሰዎች ያደርጉት የሰሩት ነው፡፡ አሁን እግዚአብሄር የሚመርጠው ዬትኛውን ነው? የዕብራዊያን ጸሐፊ እንዲህ ይላል "እንግዲህ ዘወትር ለእግዚአብሄር የምስጋናን መሥዋዕት ማለት ለስሙ የሚመሰክሩ የከንፈሮችን ፍሬ በእርሱ አቅርቡ" ይላል (ዕብራዊያን 13፡15)

በዘመናት የታወቁ የሐይማኖት መሪዎች የመካኒካል ሙዚቃን በአምልኮ ውስጥ ሳያራምዱ ኖረዋል ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚያስተምረው በመዘመር ነበር፡፡ አንዳንድ መግለጫዎቻቸውን

እናስተውል፡፡

1. ጆን ዊስሊ “ በቤታችን ውስጥ በሙዚቃ መሣሪያዎች ላይ ተቃውሞ የለኝም ካልተሰሙ እና ካልታዩ” ክላርክ ሐተታ ጥራዝ IV ገፅ 686፡፡

2. ጆን ካቪን “የእግዚአብሄርን ውዳሴ ለማክበር የሙዚቃ መሣሪያ እብደትን ከማቀጣጠል፣ የመብራት ማብራት የሌሎቹን የሕጉን ጥላዎች መልሶ ከማደስ የበለጠ ተስማሚ አይሆንም፡፡ ስለዚህ መጥመቂያን ሌሎችን ብዙ ነገሮችን ከአይሁድ ወስዷል” የጆን ካልቪን ሐተታ ሣላሣ ሶስተኛው መዝሙር

3. ማርቲ ሉተር “ኦርጋን የባአል ምልክት ነው” ሲል ጠርቶታል፡፡ ማክሊንቶክ እና የጠንካራ ኢንሳይክሎፔዲያ ሙዚቃ ጥራዝ VI ገፅ 762፡፡

4. አዳም ክላርክ “ሙዚቃን እንደሳይንስ እወደዋለሁ እና አደንቃለሁ ነገር ግን በእግዚአብሄር ቤት ውስጥ ያሉትን የሙዚቃ መሣሪያዎች እፀየፋለሁ እና እጠላለሁ፡፡ ይህ ሙዚቃን አላግባብ መጠቀም ነው፡፡ እናም እዚህ በጸሃፊው በክርስቲና አምልኮ ዉስጥ እንደዚህ ካሉ ሙስናዎች ሁሉ ጥበቃዬን አስመዘግባለሁ” ክላርክ ሐተታ ጥራዝ IVገፅ 686

ሌሎች ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ምሁራንም በአምልኮ ውስጥ የሙዚቃ መሣሪያዎችን ተቃውመዋል፡፡ ነገር ግን ከዬት ተጀመረ? ከካቶሊክ ቤተክርስቲያን ጋር ተጀመረ እና ከካቶሊክ ቤተእምነት ከወጡ የሐይማኖት ድርጅቶች ባብዛኛው የመካኒካል ሙዚቃቸውን ያዙ፡፡

ብዙዎቹ የሐይማኖት ድርጅቶች በሙዚቃ መሣሪያ ስለመጠቀማቸው እንደሚከተለው ለማስረዳት ይሞክራሉ

1. ዳዊት ተጠቅሞበታል ይላሉ፡፡ ያ እውነት ሊሆን ይችላል ነገር ግን ዳዊት በአንድ ሕግ ሥር እንደኖረና እኛ ደግሞ በሌላ ሕግ ሥር እንዳለን ማስታወስ አለብን፡፡ እኛ ዳዊት ያደረገውን ስላደረገ ብቻ ማድረግ አንችልም እንደዚያ ከሆነ በዓመት አንድ ጊዜ መሥዋዕት ለማቅረብ ወደ ኢየሩሳለም ተመልሰን መሄድ አለብን ማለት ነው፡፡ እነዚህ ሰዎች ለሙዚቃ መሣሪያ ብቻ ወደ ዳዊት ይመለሳሉ ሌላውን ግን አይቀበሉትም፡፡ እኛ በሌላ ህግ ስለመሆናችን እነዚህን አንብብ (ዮሐንስ 1፡17፣ 2 ቆሮንቶስ 3፣ ዕብራዊያን 10፡9)

2. የሚሉት ሌላው ደግሞ የሙዚቃ መሣሪያ እንዳይኖራችሁ አልተባለም ይላሉ፡፡ ነገር ግን በአምልኮ ውስጥ ብዙ ነገር አይኑር አይልም፡፡ ሊኖረን የሚገባውን ልናደርግ የሚገባውን ይናገራል እንጂ ዘምሩ ብሏል (ኤፌሶን 5፡19)፣ በቃ የተባለው ይህ ነው ይህ ደግሞ ሌላ ነገር አይጨምርም፡፡

3. ምንም ችግር እንደሌለው ይናገራሉ፡፡ ሜካኒካል ሙዚቃን በቤት ውስጥ በሰርግ በመዝናኛ ወዘተ መኖሩ ምንም ስህተት ላይሆን ይችላል

ነገር ግን የአምልኮ የተለየ ነው። ጌታ ያላዘዘውን በአምልኮ ላይ መጨመር ስህተት ነው (ዮሐንስ ራዕይ 22፡18~19)

4. ለአምልኳችን ይጠቅመናል ይላሉ። ታዲያ ለምን ጌታ አላዘዘውም? እኔ ግን እጠቁምሃለሁ እርዳታ ወይም ጥቅም አይደለም ነገር ግን በሥራ ላይ ሲውል የአምልኮ አካል ነው ይህ ደግሞ ከቅዱሳት መጽሃፍት ጋር የሚስማማ አይደለም።

5. በሰማይ ሙዚቃ አለ ይላሉ። ቅዱሳት መጽሃፍት በሰማይ ሙዚቃ መሣሪያ አለ ብለው አያስተምሩም። ምንም እንኳ አለ ቢባል እኛ እንድንጠቀም አያጸድቅም። በሰማይ ውስጥ በአምልኮ ውስጥ የማይኖሩን ብዙ ነገሮች አሉ።

6. እንወደዋለን ይላሉ። መልካም ! እኔ ኬክ እወዳለሁ እንደዚሁም ለስላሳ መጠጥ እወዳለሁ። እና ያ ማለት እነዚህን የምወዳቸሁን በአምልኮ ቦታ ይዤ ሄጄ መጠቀም እችላለሁ? መልሱ አይደለም ነው። እኛ እንወደው ይሆናል ጌታስ ይፈልገዋል?

ስለዚህ ለአምልኮ በምንሰበሰብበት ገዜ በጌታ ቀን ጌታን በዝማሬ እናወድሰዋለን። ይህ ደግሞ በመንፈስና በእውነት መሆን አለበጥ ስለዚህ በመረዳትና በአክብሮት መዘመር አለብን። እንደቅዱሳት መጽህፍት መዘመር አለብን ይህ ማለት በድምጻችን ሙዚቃ መዘመር አለብን ይህ ብቻ አይደለም መዝሙሮቹ ራሳቸው መጽሃፍ ቅዱሳዊ መሆን አለባቸው።

መጽሃፍ ቅዱስ የጉባኤ መዝሙርን ያስተምራል። ማለትም ሁላችንም በመዝሙር በዝማሬ እና በመንፈሳዊ መዝሙሮች መዘመር ድምጻችንን ማጣመር እንዳለብን ያስተምራል። በእነዚህ መዝሙሮች እግዚአብሄርን እናመሰናለን። ለጌታ ታማኝ ለመሆን እርስበርሳችሁ አስተምሩና አንፁ አበረታቱ ይላልና። በመካኒካል መሣሪያዎች ጩሄት  እና ግርግር ሳይታገድ እንደዚህ ዓይነት መዝሙሮችን መዘመር ምንኛ ድንቅ ነው ነገር ግን በአክብሮት በሰላም በተረጋጋቸ ነፍሳችን የሰማይ አምላክን በጋራ እያመሰገንን ድምጻችንን ከፍ በማድረግ ከማወደስ የበለጠ ምን ተስማሚ ነገር ሊኖር ይችላል?  እግዚአብሄርም የሚፈልገው ይህንን ነው።

## ጥያቄዎች

1. የክርስቲና እምነት ምንድነው?
2. ከአዲስ ኪዳን ውስጥ ስለ መዝሙር የተጻፉትን ጥቅሶች አንብብ
3. እነዚህ ጥቅሶችህ ስለሜካኒካል ሙዚቃ ያስተምራሉ?
4. ሁለቱን የሙዚቃ ዓይነቶች ጥቀስ
5. የሰው ድምጽ ሙዚቃ ምንድነው?
6. መካኒካል ሙዚቃ ምን እንደሆነ አብራራ
7. እግዚአብሄር በምን ዓይነት እንድናመሰግነው ይፈልጋል?

8. የሙዚቃ መሳሪያን የተቃወሙ የሃይማኖት መሪዎችን ስሞች የተወሰኑትን ጥቀስ

9. በመካኒካል ሙዚቃ ማምለክ የተጀመረው ዬት ነው?

10. የሙዚቃ መሳሪያ መጠቀምን አስፈላጊ አድርገው የሰጡትን መግለጫዎቻቸው ምን ምን ነበሩ?

11. የመካኒካል ሙዚቃ ለመጠቀም ወደ ዳዊት የማንመለሰው ለምንድነው?

12. በአምልኮ ውስጥ መካኒካል ሙዚቃን ምን ያስወግዳል?

13. በቤታችን ውስጥ የሙዚቃ መሣሪያ ሊኖረን ይችላል?

14. ይህ ማለት በአምልኮም እንዲኖር የዷርገዋል?

15. ዮሐንስ ራዕይ 22፡18~19 አንብብ

16. ጌታ የምንወደውን ነገር ወይም ደስ ያለንን ነገር ወደ አምልኮ ቦታ ብናመጣው ያጽድቅልናል?

17. በሰማይ የሙዚቃ መሣሪያ ይኖራል?

18. ምን ዓይነት መዝሙር እንድንዘምር ጌታ የሚፈልገው?

19. የጉባኤ መዝሙር የሚለውን አብራራ

20. የምንዘምርበትን ምክንያት ጥቂት ግለፅ

## ትምህርት አሥራ አንድ
## የጌታ እራት

ሌላው የአምልኮ ተግባር የጌታ እራት ነው። ክርስቶስ ሰው በጣም የሚረሣ መሆኑን ያውቃል። ስለዚህ ለማስታወስ የሚረዳውን ነገር ወደ ኃላ ሊስቀርላቸው ፈለገ። ይህም የጌታ መታሰቢያ ወይም የጌታ እራት በመባል ይታወቃል።

ወደ ፊት ከመሄዳችን በፊት በመጀመሪያ ይህ ነገር እንዴት እንደተቋቋመ እንመልከጥ አብረን ወደ ማቴዎስ 26፡26~28 እንሂድ “ሲበሉም ኢየሱስ እንጀራን አንሥቶ ባረከ ቆርሶም ለደቀመዛሙርቱ ሰጠና እንካችሁ ብሉ ይህ ሥጋዬ ነው አለ። ጽዋንም አንሥቶ አመስግኖም ሰጣቸው እንዲህም አለ። ሁላችው ከእርሱ ጠጡ ስለብዙዎቸ ለኃጥያት ይቅርታ የሚፈስ የአዲስ ኪዳን ደሜ ይህ ነው” አላቸው (ማቴዎስ 26፡ 26~28) ይህ ምን ያህል ቀላል እንደነበረ እባክዎ ልብ ይበሉ። ክርስቶስ እንጀራ ሥጋውን እንደሚወክልና ሥጋውን በማስታወስ መካፈል እንዳለበት አመልክቷል። የወይኑ ፅዋ ወይም የወይን ፍሬ ጭማቂው ደሙን እንደሚወክልና የደሙ መታሰቢያ ይሆን ዘንድ መካፈል እንዳለባቸው ተናግሯል። በሌላ አነጋገር ክርስቶስ ደቀመዛሙርቱ በመስቀል ላይ የሚከፍላቸውን መስዋዕትነት እንዲረሱት አልፈለገም። ስለዚህም በየጌታ ቀን ኅብስቱንና ፅዋውን ሲበሉ ሥጋውንና ደሙን በማሰብ ያን ጊዜ በአዕምሯቸው አዲስ ኪዳን ይሆናል።

ወደ 1ኛ ቆሮንቶስ 11:20~29፣ እንሂድና ጳውሎስ የሚለውን እናንብብ "እንግዲህ አብራችው ስጸበሰቡ የምትበሉት የጌታ እራት አይደለም በመብላት ጊዜ እያንዳንዱ የራሱን እራት ይበላልና አንዱም ይራባል አንዱ ግን እበላልና፣ አንዱም ይራባል አንዱ ግን ይሰክራል። የምትበሏቸውና የምትጠጡባቸው ቤቶች የላችሁምን? ወይስ የእግዚአብሄርን ማህበር ትንቃላችውን? አንዳችም የሌላቸውን ታሳፍራላችውን? ምን ለበላችሁ? በዚህ ነገር ላመስኛችሁን? አላመሰግናችውም። ለእናንተ ደግሞ አሳልፌ የሰጠሁትን እኔ ከጌታ ተቀብያለሁና ጌታ ኢየሱስ አልፎ በተሰጠባት በዚያች ሌሊት እንጀራን አንስቶ አመሰገነ ቆርሶም እንካቸሁ ብሉ ይህ ስለ እናንተ የሚሆን ሥጋዬ ነው። ይህን ለመታሰቢያዬ አድርጉት አለ። እንዲዚሁም ከእራት በኃላ ፅዋውን ደግሞ አንስቶ ይህ ፅዋ በደሜ የሚሆን አዲስ ኪዳን ነው። በጠጣችውት ጊዜ ሁሉ ይህን ለመታሰቢያዬ አድርጉት አለ። ይህን እንጀራ በበላችሁ ጊዜ ይህን ፅዋ በጠጣችው ጊዜ ሁሉ ጌታ እስኪመጣ ድረስ ሞቱን ትናገራላችሁና። ስለዚህ ሳይገባው ይህን እንጀራ የበላ ወይም ይህን ፅዋ የጠጣ ሁሉ የጌታ ሥጋና ደም ዕዳ አለበጥ ሰው ግን ራሱን ይፈትን እንዲሁም ከእንጀራው ይብላ ከፅዋውም ይጠጣ። ሳይገባው የሚጠጣ ና የሚበላ የጌታን ሥጋ ስለማይለይ ለራሱ ፍርድ ይበላልና ይጠጣልምና" (1 ኛ ቆሮንቶስ 11:20~29)፣ አሁን በመጀመሪያ ጳውሎስ ክርስቲያን ወንድሞችን የጌታን እራት ስላደረጉበት መንገድ ገሰጻችው። ጌታ ባዘዘው መንገድ ከተካፈሉት ይልቅ ጠግበው ሊጠጡና ሊሰክሩበት ወደሚበሉበት ግብዣ አደረጉጥ ይህ በፍጹም የታሰበ አልነበረም። ይልቁንም ዓላማውንና መካፈል ያለባቸውን መንገድ ያሳያቸዋል። ጳውሎስ እነዚህን ሁሉ መረጃዎች ከጌታ እንዲቀበሉ አሳስቦአቸዋል እና ሃሳቡ እነዚህ ነበሩ።

1. ጌታ አልፎ በተሰጠበት ሌሊት እራትን አዘጋጀ
2. እንጀራውም የተቆረሰ ሥጋውን እንዲያስታውሳቸው አመለከተ
3. እንዲሁም ፅዋውን አንሥቶ ይህን የደሜ መታሰቢያ በማድረግ እንዴት እንዲካፈሉ አሳይቷል
4. በተካፈሉበት ጊዜ ሁሉ ጌታ እስኪመጣ ድረስ ሞቱን እንዲታሰብ አሳይቷል
5. ብቁ ሳይሆኑ ከራት የሚካፈሉት የክርስቶስ ሥጋና ደም ባለዕዳ ናቸው
6. እያንዳንዱ ራሱን መርምሮ ከዚያም ይካፈል
7. ሳይገባቸው የሚበሉና የሚጠጡ ለነፍሳቸው እርግማን ይበላሉ ይጠጣሉም

ስለዚህ እሱ ያነሳቸው ዋና ዋና ነጥቦች እነዚህ ናቸው እና በጥንቃቄ ብንመረምራቸው ጥሩ ነው

ጥናታችንን ስንቀጥል ልናስታውላቸው የምንፈልጋቸው በርካታ ነገሮች

አሉ፡፡

1. ጌታ አንድ ፅዋ ብቻ መጠቀም እንዲሚቻል አያስተማረ አይደለም፡፡ አንዳንድ ጊዜ ሁሉም ቡድኖች የጌታን እራት ለመመገብ አንድ ኩባያ ብቻ ጥቅም ላይ ሊውል ይችላል ብለው ይደመድማሉ እናም ቡድናቸው በሙሉ ካንድ ፅዋ ጠጥተው ይጨርሳሉ፡፡ ጌታ በመያዣው ውስጥ ያለውን ይዘት እንጂ መያዣ ዕቃውን እያጎላ አልነበረም፡፡ የክርስቶስን ደም በማሰብ እስከተካፈሉ ድረስ አሁን በአንድ ወይም ብብዙ ትንሽ ለውጥ አያመጣም፡፡ አንድ ጊዜ አንድ ሰው አንድ ፅዋ ወደሚያምኑት ጉባኤዎች ጎብኝቶ ነበር ስላዚህ ያ የፅዋ ዕቃ እየተላለፈ እሱ ጋ ሲደርስ በውስጡ ያለውን የወይን ፍሬ ጭማቂውን ሁሉ ጠጣ ከዚያም ሁሉንም ጠጥቷል ብለው ተቃወሙት እና የቀረው ጉባኤ ምን ያግኝ? ጌታ ሁሉንም ጠጡ" ያለውን አስታእሳቸው፡፡ ይህ የሚያመለክተው ሰዎች እንደፅዋ ቀላል በሆነ ነገር እንዴት እንደሚታለሉ ብቻ ነው፡፡ ምንም እንኳን አንድ ፅዋ መጠቀሙ ቅዱስ መጽሐፋዊ ባይሆንም ለጤና ዓላም እና ለሌሎች ምክንያቶች ግን የግለሰብ ኩባያዎችን መጠቀም የተሻለ ይሆናል፡፡

2. የጌታን እራት በመመገብ የክርስቶስን ሥጋና ደም ከማሰብ በተጨማሪ ብጌታ ዳግም ምጻዓት የሚያምኑ ሕዝቦች እዚህ እንዳሉ ለአንድና ለሁሉም ማሳሰቢያም ነው፡፡ ይህ ባይሆን ኖሮ አይካፈሉም ነበር፡፡

3. የጊታ እራት መካፈል እያንዳንዱ ሰው ባሳለፈው የሳምንቱ ህይወት ወይም ያለፉት በርካታ ሣምንታ በጉባኤው ታማኝ ካልሆነ እና መንፈሳዊነቱ ምን እንደሆነ ለማወቅ ራሱን የሚመረምርበት ጊዜ ነው ሁኔታውን መመርመር አለበት በተቻለ መጠን ለጌታ ታማኝ ሆኖ እየኖረ መሆኑን ካወቀ ከዚያ አስቀድሞ ሂዶ የጌታን እራት መካፈሉ ተፈጥሮአዊ ነው፡፡ ነገር ግን በህይወቱ ኃጥያቶች እንዳሉ ካወቀ በመጀመሪያ ከነሱ ንስሃ መግባት እና አስፈላጊውን እርማት ምድረግ እና ከዚያም የጌታን እራት ለመውሰድ ዝግጁ ነው፡፡

4. አንድ ሰው ራሱን ሳይመረምር ቀርቶ እራቱን ቢበላና ቢጠጣ እና ለዘላለም የሚድን ሳይሆን ለእርግማን ይሆናል፡፡ በርግጥ እኛ ሁላችንም ፍፁማን አይደለንም ኃጥያት ይኖረናል፡፡ ነገር ግን ጌታ እኛ ፊጹማን እንዳልሆንን ያውቃል እናም እኛ የምንችለውን ሁሉ ስናደርግ ጥሩ ነው እሱም ይረዳናል፡፡ እናም ከንሰሃ ቦኃላ እንድንካፈል እንበረታታለን፡፡ ነገር ግን አንድ ግለሰብ ሆን ብሎ በግድየለሽነት ኃጥያትን ከሠራ የጌታ እራትን ለመካፈል አልተዘጋጀም እና እራሱንም ሆነ ሌሎቹን እያታለለ ነው ነገር ግን ጌታ ያውቀዋል፡፡ እናም መንፈሳዊ ህይወቱን በቅዱሳት መጽሃፍት አስተካክሎ መካፈል አለበት

5. የተዘጋ ኅብረት ሊኖረን አይገባም፣ እና ስለዚህ ከተወሰነ ቁጥር በስተቀር ሁሉም እንዲካፈሉ አንፈቅድም፣ ቅዱሳት መጻፍት ራሳችንን በምንመረምርበት መሰረት አስቀምጧል የቤተክርስቲያን አባል ያልሆነ ሰው

ሊወስድ አይችልም። እውነትን ሲያውቅ ይታዘዛል ያለዚያ ሳይታዘዝ ይህን የምንሰጥ ከሆነ ፈጽሞ ሊታዘዝ አይችልም።

በማጠቃለያ በሐዋርያት ሥራ 20፡7 ላይ የጥንቶቹ ክርስቲያኖች በሣምንቱ የመጀመሪያ ቀን እንጀራውን ለመካፈል ሲሰበሰቡ እናነባለን ስለዚህ እኛም በተመሳሳይ ማድረግ አለብን ግን የሣምንቱ የመጀመሪያ ቀን ዬትኛው ነው? በያንዳንዱ የሣምንቱ የመጀመሪያ ቀን  አንተን ወይም እኔን ሌላውንም የጌታን እራት የምንበላበት የጌታ ቀን እንድትሆን የሣምንቱን የመጀመሪያ ቀን እንድፀጋጅ ማን ሥልጣን ሰጠን?  ማንም ። ስለዚህ እግዚአብሄር እንደተወው እንተውና የቀድሞዎቹ በሳምንቱ የመጀመሪያ ቀን ተሰብስበው ይሰግዱ ነበር ያመልኩ ነበር ይህ ደግሞ የጌታ እራትን ይጨምራል።

## ጥያቄዎች

1. የጌታ እራትን ያቋቋመው ማን ነው?
2. ማቴዎስ 26፡26~28 አንብብ
3. እንጀራን ወይም ሳብስትን የምንቆርሰው ለምንድነው?
4. የወይን ጭማቂ ምንን ይወክላል?
5. ደቀመዛሙርቱ ምን ያህል ጊዜ ይካፈሉ ነበር?
6. 1 ኛ ቆሮንቶስ 11፡20~29 አንብብ
7. የቆሮንቶስ ሰዎች በጌታ እራት ጊዜ ምን አደረጉ?
8. ጳውሎስ በዚህ ጉዳይ ምን አደረገ?
9. ጳውሎስ የገታ እራትን ጉዳይ ከዬት ተቀበለ?
10. የጌታን ሞት በጌታ እራት በመካፈል እንደገና እስኪመጣ ድረስ እንዴት እንደሚገለጥ አስረዳ
11. ሳይገባቸው ቢካፈሉ ምን ይሆናል?
12. ቅዱሳት መጽሃፍት ከአንድ ኩባያ ሁሉም እንዲጠቀሙ ያስተምራል?
13. በመያዣው ላይ ያለው አጽናኦት ነው ወይስ ብመያዣው ወስጥ ያለው ይዘት ነው ተፈላጊው?
14. የጌታ እራት ከጌታ ዳግም መምጣት ጋር ያለው ዝምድና ምንድነው?
15. የጌታ እራት ለእያንዳንዳቸው ለሚካፈሉ ክርስቲያኖች የግል በረከት ሊሆን የምችለው እንዴት እንድሆነ ግለጽ
16. ጌታ እራቱን ከመውሰዳችን በፊት ፊጹም እንድንሆን ይፈልጋል?
17. አንድ ሰው ሆን ብሎ ኃጥያት ከሠራ መካፈል ይችላል?
18. የጌታ እራት መካፈል እንደማይገባው እኛ ለሰው መናገር እንችላለን?
19. ከሳምንቱ በዬትኛው ቀን ነው ክርስቲያኖች ኢገታ እራት

ለመካፈል የሚሰበሰቡት?

20. ከሣምንቱ የመጀመሪያ ቀን የጌታን እራት ይበላ ዘንድ ጌታ ሥልጣን ሰጥቶአል?

## ትምህርት አሥራ ሁለት
## ስጦታ

ወደ አዲስ ኪዳን አምልኮ የመጨረሻው ተግባር ደርሰናል እርሱም መስጠት ወይም በስጦታ ማምለክ ነው።መጽሃፍ ቅዱስም የሚያስተምረው ይህንን ነው።ሆኖም ብዙ ሰዎች ስለዚህ ጉዳይ በጣም አያውቁም ስለዚህ ጉዳይ ምን እንደሚሉ ለማየት እንፈልጋለን። የቅዱሳት መጽሀፍቶች አንዳንድ ቁልፍ ምንባቦችን በማስተዋል እንጀምራለን።

ወደ 1ኛ ቆሮቶስ 16፡1~2 አብረን እንሄዳለን "ለቅዱሳንም ገንዘብን ስለማዋጣት ለገላቲያ አብያተክርስቲያናት እንደደነገግሁት እናንተ ድግሞ እንዲሁ አድርጉ። እኔ ስመጣ ይህ ገንዘብ ማዋጣት እንዳይሆን ከናንተ እያንዳንዱ በየሣምንቱ ብፊተኛው ቀን እንደቀናው መጠን እያስቀረ በቤቱ ያስቀምጥ" (1ኛ ቆሮንቶስ 16፡~2)። አሁን ወደ ፊት ከመሄዳችን በፊት እሱ የሚያነሳቸውን ነጥቦች እንዚህን ጥቅሶች እንመርምር

1. ይህ ስጦታ በሣምንቱ የመጀመሪያ ቀን መደረግ አለበጥ ለምን ክርስቲያኖች ለአምልኮ የሚሰበሰቡበት ቀን በመሆኑ ስብስቡ የሚሰበሰብበት የተመረጠበት ጊዜ ነበር። ግን ሌላ ቀንስ ? ስለ ሌሎች ቀናት ምንም የተነገረ ነገር የለም። ይህ ትዕዛዝ በሣምንቱ የመጀመሪያ ቀን እንዲሆን ተገልጿል። አሁን በተለያዩ የሃይማኖት ቡድኖች በቀኑ የሚያገኟቸው ጊዜያት ቢኖሩም በተሰበሰቡ ቁጥር ይሰበሰባሉ። ነገር ግን ይህ የተለተ ድርጊትነው መጽሐፍ ቅዱሳዊ አይደለም። የክርስቶስ አብያተክርስቲያናት በእያንዳንዱ የሣምንቱ የመጀመሪያ ቀን ይገናኛሉ እናም አባላት ለመስጠት የሚጠበቅባቸውም ቀን በዚህ ቀን ነው።

2. ሁሉም ክርስቲያኖች እንዲጡ ይጠበቅባቸዋል። በርግጥ ይህ ከሣምንት ብፊት የበለጸጉ ከሆነ ነው ጌታ ህዝቡ ምንም ነገር ካላገኙ እንዲሰጡ አይጠብቅባቸውም። ነገር ግን ከቻሉ እንዲሰጡ ይጠብቃል። እያላቸው እምቢ ማለት ግን ኃጥያት ነው።

3. እንዳገኙት በቤታቸው ያስቀምጡ። በዚያን ጊዜ አትክልት ከብቶች ወይም ሊኖራቸው የሚችለውን ሁሉ ይሰጡ ነበር ማለት ነው። እንዲሁም ገንዘብም ይሰጣሉ። ዛሬ እኛ ብዙውን ጊዜ ገንዘብ እንሰጣለን ምክንያቱም ብዙ ሰዎች ያላቸውን ወደ ገንዘብ ስለሚለውጡ እና በሣምንቱ ገንዘብ ለማግኘት ስለሚሠሩ። ነገር ግን እንደየቦታው ይወሰናል እንደየሁኔታው ነው መዋጮው በገንዘብም ሆነ ባለው ሊሆን ይችላል።

4. እንዴበለጸጉ መስጠት ነበረባቸው። ይህም እንዴገቢያቸው መጠን መሆን አለበጥ ግን ያህል ከገቢያቸው ይሰጣሉ? ያ የእነርስይ ውሳኔ ነው ዛሬም እውነቱ ይህ ነው አዲስ ኪዳን አሥራትን አያስተምርም ወይም ከአንድ አሥረኛው የሚባል አያስተምርም። አይሁድ ከኖሩት ሕግ እጅግ በሚሻል ሕግ ሥር እስከኖርን ድረስ ከእነሱ የሚበልጥ ከአንድ አሥረኛው የሚበልጥ መስጠት እንችላለን ታዲያ የሚሻል ሕግ ካለን የሚሻል ተስፋ ካለን ለምን አብዝተን አንሰጥም? ጌታ በበለጸንበት መጠን እንድንሰጥ ይፈልጋል። የበለጸጋቸውበትን ታውቃላቸው እና ምን ያህል መስጠት እንዳለባቸው ታውቃላቸው ነገር ግን በሁሉም ዕድል ከሣንትም ይልቅ የወረቀት ገንዘብ መስጠት መቻል አለበጥ እና በአጠቃላ ከልባችን መስጠት እንዳለብን አምነን ለማስጠት የምንጀምርበት ጊዜ አሁን ነው። አትማማም?

5. እሱ ሲመጣ ምንም ዓይነት ስብሰባ እንዳይኖር ሄዴው መስጠት ነበረባቸው። በሌላ አገላለፅ ይህንን ምክር ቢከተሉ ኖሮ በመጣ ጊዜ ሁሉም ነገር ቀድሞ ተጠብቆለት የነበረውን ፍላጎት ለመንከባከብ ይችል ነበር። ዛሬም ተመሳሳይ ነው። ጌታ እንዳሰበ ከሰጠን የጌታን ሥራ ለመቀጠል አስፈላጊ ገንዘብ ይኖረናል አሁን በሃይማኖታዊው ዓለም ውስጥ አብዛኞቹ አብያተክርስቲያናት ይህንን ትምህርት አይከተሉም ስለዚህም ያለማቋረጥ ገንዘብ ይለምናሉ። ራሳቸው ከመስጠት ይልቅ እርዳታ ለመለመን ወደ ዓለም ይወጣሉ። አንዳንዶቹ መጽሔት ይሸጣሉ አንዳንዶቹ ባዛር አላቸው አንዳንዶቹ መዝናኛ ላይ ይፈጥራሉ ነገር ግን የቤተክርስቲያን ፍላጎቶች እንዲሟሉ ጌታ ህዝቡን እንዲሰጡ አዟል። ይህ የጌታ መንገድ ነው እና እሱ ከሱስ ውጪ ቃሉን ሊለውጥ ወይም ሊያሻሽል ማንም አይችልም።

አሁን ስለመስጠትን በሚመለከት ሌላ ጥቅስ እናስተውል “ይህንም እላለሁ በጥቂት የሚዘራ ድግሞ በጥቂት ያጭዳል በበረከትም የሚዘራ በበረከት ደግሞ ያጭዳል እግዚአብሄር በደስታ የሚሰጠውን ይወዳልና እያንዳንዱ በልቡ እንዳሰበ ይስጥ በሃዘን ወይም በግድ አይደለም” (2 ቆሮንቶስ 9፡6~7)። እስቲ የሚከተሉትን ተመልከተ

1. ጳውሎስ በዘራነው መንገድ እናጭዳለን ይላል። ትንሽ ከዘራን ትንሽ እናጭዳለን። ብዙ ከዘራን ብዙ እናጭዳለን አሁን ይህ እርሻ ንግድና በሁሉም የህይወት ዘርፎች ነው። በጌታ ሥራም እውነት ነው። ሳትሰጡ ከቤተክርስቲያን መውሰድ አይቻልም። አብዛኞቻችን ጌታን በቃሉ እንወዴዋለን ብለን እንዳናምን እፈራለሁ። እኛ ግን እሱን መሞከር አለብን። ብዙ በሰጠን መጠን ብዙ እንደምንቀበል እውነት መሆኑን ወይም እንደምናገኝ እርግጠኛ ነኝ። ቃሉ ብሏልና።

2. እያንዳንዱ በልቡ እንዳሰበ መስጠት እንዳለበት ተናግሯል። ወደ አምልኮ ከመምጣታችን ብፊት ምን ያህል መስጠት እንዳለብን አስቀድመን ወስነን መሆን አለበጥ እሱ እየተናገረ ያለው ይህ ነው።

ለመስጠት ጊዜ እስኪደርስ ድረስ  አትጠብቅ እና ቀድመህ ያዘጋጀኼውን አንስተህ ወደ መሰብሰቢያ ሳህን ውስጥ ማስገባት ነው ይላል። መስጠት የሚችሉትን ቀድመው ካወቁ እሱኑ ይስጡ።

3. አንድ ሰው በሃዘን መስጠት እንደሌለበት ይናገራል። ማለትም ለመስጠት መገደድ ወይም ሃዘን ሊሰማዎት አይገባም። መስጠት ሳትወድ በግድ ወይም ሳትፈልግ ከሰጠህ ስጦታህ በጌታ ዘንድ ዋጋ የሌለው ከንቱ ይሆናል።

4. አንድ ሰው መስጠት አስፈላጊ እንደሆነ ስለሚሰማው መስጠት እንደሌለበት ይናገራል። ጌታ በርግጠኝነት መስጠት እንደሌለብህ ወደምታስብበት ሁኔታ ሊያስገድድህ እየሞከረ አይደለም

5. ይልቁንም እግዚአብሄር በደስታ የሚሰጠውን ይወዳል ይላል። አንተ እንዴት እንድሰጥ ይፈልጋል? በደስታ እንድሰጥ ይፈልጋል። ምክንያቱም ስለፈለጋችሁ እናም  ማድረግ በመቻላችሁ ደስተኞችም ስለሆናችሁ እግዚአብሄር ዘንድ ተወዳጅ ናችሁ። ስለዚህ ሁልጊዜ እንደዚህ ዓይነት ሰጪዎች መሆን አለብን

አሁን በመዝጊያው ላይ ጌታ ራሱ ከመቀበል ይልቅ የሚሰጥ ብጸዕና እንዳለው መናገሩን አስታውስ (የሐዋሪያት ሥራ 20:35)  እኔ ደግሞ እኛ ከሚሰጥ ይልቅ የሚቀበል ብጸዕና አለው እያልን እንዳይሆን እፈራለሁ። ምክንያቱም አብዛኞቻችን ስግብግብ ስስታሞች ራስ ወዳድ ነን። ስለዚህም እግዚአብሄርን ለእርሱ የሚገባውን እንዘርፋለን። እግዚአብሄር ይርዳን ከንቅልፋችን እንድንነቃ እና ካለን ነገር የተውሰነውን ለእርሱ በእውነት ለእርሱ የሆነውን ልንመልስ እንጀምር በቅዱሳት መጽህፍት እንዴት መስጠት እንዳለብን እስክንማር ድረስ ልንሆን የሚገባን ዓይነት ክርስቲያኖች ልንሆን አንችልም።

## ጥያቄዎች

1. መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ስጦታ ያስተምራል?
2. አብዛኞቹ ሰዎች እንደሚገባቸው ይሰጣሉ?
3. 1ኛ ቆሮንሮስ 16፡1~2 አንብብ
4. ክርስቲያኖች ለስጦታ የሚሰጡት ቀን መቼ እንደሆነ ስጥ
5. ሌሎቹ ቀናቶችስ ስጦታን በተመለከተ እንዴት ናቸው?
6. የተለያዩ የሐይማኖት ድርጅቶች ምን ያህል ጊዜ መዋጮ ያደርጋሉ?
7. ሁሉም ክርስቲያኖች መስጠት ይጠበቅባቸዋል?
8. አንዳንዶች መስጠት ካልቻሉስ ምን ይሆናል?
9. ሕዝቦቹ የሚሰጡትን ካላገኙ ጌታ እንዲሰጡ ይጠብቅባቸዋል?
10. ሕዝቦቹ የሚሰጡትን ካገኙ ወይም ከበለጸጉ ጌታ እንዲሰጡ ይጠብቅባቸዋል?

11. ምንድነው የሚሰጡት?
12. ምን ያህል ነው የሚሰጡት?
13. አዲስ ኪዳን ስለ አሥራት ያስተምራል?
14. ከአንድ አሥረኛ በላይ መስጠት ያለብን ለምንድነው?
15. ሰዎች ብዙውን ጊዜ ለሚፈልጉት ነገር በቂ ገንዘብ አላቸው?
16. ለምንድነው ለጌታ ብዙ የማይኖረን?
17. ክርስቲያኖች ለምን መስጠት እንዳለባቸው ግለፅ
18. ሌሎቹ የሐይማኖት ድርጅቶች ገንዘብ የሚሰበስቡት እንዴት ነው?
19. ይህ አሰባሰብ ጌታ ሕዝቡ እንዲሰበስብ የፈለገው እንዲህ ነው?
20. 2 ቆሮንቶስ 9፡6~7 አንብብ
21. የመዝራትና የማጨድን መርሆ ግለፅ
22. ለምንድነው ብዙዎቻችን ብዙ የማናጭደው?
23. እንደቀናን መጠን መስጠት አለብን ማለት ምን ማለት ነው?
24. ጌታ በኅዘን እንድንሰጥ ይፈልጋልን ወይስ በግድ? ግለፅ
25. እግዚአብሄር ምን ዓይነት ሰጪ ይወዳል?
26. ማን ነው "ከሚቀበል ይልቅ የሚሰጥ የተባረከ ነው" ያለው?
27. አብዛኞቹ ክርስቲያኖች መስጠትን በተመለከተ ምን እንደሆነ ግለፅ

## ትምህርት አሥራ ሦስት
## በጉባኤ ላይ መገኘት

በክርስቲያኖች ከሚፈጸሙ በጣም አሳዛኝ ስህተቶች አንዱ በቤተክርስቲያን ጉባኤዎች ላይ አለመገኘት ነው። ከሌሎች ወንድሞች ጋር ለአምልኮ ለመገናኘት በቂ አክብሮት ከሌለው እንዴት ሰው ለጌታ ታማኝ ለመሆን ተስፋ ያደርጋል? ቁምነገሩ እንዲህ ባለ ሁኔታ ውስጥ ታማኝ መሆን አይችልም።

ብዙዎቹ የሐይማኖት ድርጅት ሰዎች በዓመት ሁለት ጊዜ ብቻ የአምልኮ ሥርዓትን ያደርጋሉ። ይህም ገና እና ፋሲካ ነው። ሁለቱም በእግዚአብሄር ቃል ውስጥ የሉም። ነገር ግን ጌታን ለማስደሰት ይህ ብቻ አስፈላጊ ነው ብለው ራሳቸውን እያታለሉ ያሉ ብዙዎች አሉ። እነዚህ ጌታ ማን ነው ብለው ያስባሉ? ነገር ግን ብዙ የቤተክርስቲያን አባላት አልፎ አልፎ ወደ አምልኮ አይሄዱም። አንድ ሰበብ ያቀርባሉ እነሱ እንዳይገኙ የሚከለክለው ሥራቸው ነው ወይም ርቀቱ ነው ይህ ነው ያ ነው እያሉ ሰበብ ያበዛሉ። መነሳት የለበት ጥያቄ ግን ጌታ እነዚህን ሰበቦች ይቀበላልን? ፊጹም አይቀበልም። ነገር ግን እነዚህ ግለሰቦች ወደ አምልኮ አይሄዱም በሌላ በኩል ግን የሚፈልጉትን ይዘው ወደ ቤታቸው ይገባሉ ምንም ቢርቃቸው ወደ ሥራቸው መሄድ ይችላሉ ወዘተ

መገኘት ካልቻሉት መካከል አንዳንዶቹ ብዙውን ጊዜ ይህንን አስተያየት ይዘው ይመጣሉ፡፡ “ነገር ግን ጸሎቴን ብቤት ውስጥ አደርጋለሁ” ይላሉ፡፡ ነገር ግን ጌታ የሚፈልገው ያ ብቻ ነው? አይደለም ሕዝቦቹ በሣምንቱ የመጀመሪያ ቀን እንዲሰበሰቡ ጠይቋል፡፡ ይህን ሲያደርጉ ይፀልያሉ፣ ያጠናሉ፣ ከጌታ እራት ይካፈላሉ፣ እና የአቅማቸውንም ይሰጣሉ፡፡አሁን በቤታቸው ብቻቸውን ለማምለክ የሚሞክሩት ስጦታቸውን ለማን ያበረክታሉ? የጌታ እራትስ? አይ ! እኔ እርግጠኛ ነኝ እነዚህ አብዛኞቹ ግለሰቦች ለጌታ የሚያቀርቡት አምልኮ ውስጥ ከጸሎት ያለፈ ነገር አያገኙም ያን ያህል ከደርሱ ግን ወደ እግዚአብሄር ከመጸለይ የበለጠ ማምለክ እንዳለ መማር አለባቸው፡፡

ክርስቲያኖች እንደ መታመም እና ሌሎች በአምልኮ ሥርዓቶች ላይ እንዳይገኙ የሚያደርጓቸው በቅድመ ዝግጅት የሚያደናቅፏቸው ጊዜያት እንዳሉ እውነት ነው፡፡ በዚህ ሁኔታ አንድ ሰው ላለመገኘት ሰበብ ማቅረብ አይኖርበትም ይልቁንም ምክን ያት አለው፡፡ ከዚህም በላይ ጌታ የአንድን ሰው በቂ ምክን ያት ይቀበላል፡፡

አሁን ግን የአምላክ ቃል በጉባኤዎች ላይ ስለመገኘት ምን እንደሚል እናስተውል የዕብራዊያን ጸሐፊ ሲናገር “የተስፋን ቃል የሰጠው የታመነ ነውና እንዳይነቃነቅ የተስፋችንን ምስክርነት እንጠብቅ ለፍቅርና ለመልካምም ሥራ እንድንነቃቃ እርስበርሳችን እንተያይ በአንዳንዶችም ዘንድ ልማድ እንደሆነው መሰብሰባችንን አንተው እርስበርሳችን እንመካከር እንጂ ይልቁንም ቀኑ ሲቀርብ እያያቸሁ አብልጣቸው ይህን አድርጉ፡፡ የእውነትን እውቀት ከተቀበልን ቦኃላ ወደን ኃጥያት ብናደርግ ከንግዲህ ወዲህ ስለ ኃጥያት መሥዋዕት አይቀርልንምና የሚስፈራ ግን የፍርድ መጠበቅ ተቃዋሚዎችንም ሊበላ ያለው የእሳት ብርታት አለ” (ዕብራዊያን 10፡23~27) አሁን እነዚህን ዋና ዋና ነጥቦች እንይ

1. ከእኛ ጋር ባለው ግንኙነት ታማኝ ከሚሆነው ጋር እስከሆንን ድረስ ታማኝ መሆን አለብን
2. እርስበርሳችን በመረዳዳት ሁልጊዜ በበጎ ሥራ እንቀጥል
3. መሰብሰባችንን መተው የለብንም፡፡ አንዳንዶች ነበሩ እና አንዳንዶች ዛሬ ስብሰባዎችን ትተዋል፡፡ ነገር ግን ይህ የጌታ ፈቃድ አይደለም
4. ቀኑ እየቀረበ ስናይ እርስ በርሳችን መመካከር ወይም መበረታታት አለብን፡፡ ይህ ራሳችንን ለእሱ እንድናዘጋጅ ለመጠቆም ነው ይህንን ለማድረግ አንድ ሙሉ ሣምንት አለን
5. እውነትን ከተማርን ቦኃላ ወደን ኃጥያት ከሠራን ከዚያ ቦኃላ ለእኛ ምንም መስዋዕትነት እንደሌለና ክፍርድ በቀር የምንጠብቀው ምንም ነገር እንደሌለ መዘንጋት የለብንም፡፡ ይሄውም ወደ አብያተክርስቲያባት ሄደን ልናደርገው የሚገባንን ሳናደርግ ከናቅነው

እግዚአብሄር እንዴት አድርጎ ያድነናል? ስለዚህም በዚህ መልኩ መኖራችንን ከቀጠልን እንጠፋለን፡፡

ይህ ሁሉ ጌታ ወደ ቤተክርስቲያን ጉባኤያት እንድንሄድ እጠብቅብናል እና ይህ ትልቅ ጉዳይ ነው አደገኛም ነው ሁላችንም ካልቻልን ግን ለምን እንዲህ እንድናደርግ ተፈለገ? ለምን አምልኮ ላይ እንድንገኝ አስፈለገ? ብዙ ምክንያቶች አሉ አንዳንዶቹን አሁን እናስተውል፡፡

1. ምክንያቱም በትዕዛዝ እና በምሣሌ ተምረናል፡፡ በዕብራዊያን 10፡25 መሰብሰባችንን እንዳንተው አስቀድመን አንብበናል፡፡ ከዚያም ሐዋሪያት 2፡42 ላይ የቀድሞቹ ክርስቲያኖች ለአምልኮ መሰብሰባቸውን አይተናል በሐዋሪያት 20፡7 ላይ ጳውሎስ እና የጢሮአዳ ክርስቲያኖች በሣምንቱ የመጀመሪያ ቀን ለአምልኮ መሰብሰባቸውን እናያለን ስለዚህ እኛም እንዲሁ ማድረግ አለብን፡፡

2. እግዚአብሄርን ለማምለክ በጉባኤ መገኘት አለብን፡፡ ክርስቶስ በዮሐንስ 4፡23~24 ላይ እግዚአብሄር እውነተኛ አምላኪዎችን እንደሚፈልግ እና እግዚአብሄር መንፈስ እንደሆነ እና እርሱን በመንፈስና በእውነት ማምለክ እንዳለብን ነግሮናል

3. የጌታን እራት መካፈሉን የክርስቶስን ሞት እናስታውስ ዘንድ ጌታ በጉባኤ እንድንገኝ ይፈልጋል፡፡ የምንቆርሰው የምንካፈልው ዳቦ የጌታን ሥጋ የምንጠጣው ወይን ጭማቂ ደሙን ለማስታወስ ለማሰብ እንደምንወስድ ተምረናል (1ኛ ቆሮንቶስ 11፡24~25) ታዲያ በሳምንቱ የመጀመሪያ ቀን በጉባኤ ላይ የማንገኝ ከሆነ እንዴት ሥጋና ደሙን ልናስብ እንችላለን?

4. ሠርተን ከምናገኘው በስጦታ ለማለክ በጉባኤ ላይ እንገኛለን፡፡ (1ኛ ቆሮንቶስ 16፡1~2) ጳውሎስ እንደተናገረው ከሳምንቱ የመጀመሪያ ቀን ለዚህ ስጦታም መገኘት አለብን እንግዲህ የምንቀር ከሆነ እና ሁሌም የሚቀሩ ሁሉ ይህንን ዕድል የማይጠቀሙ እና ኃላፍነትም የማይሰማቸው ናቸው፡፡

5. ጌታ በጉባኤ መሃል ከእኛ ጋር እንደሚሆን ቃል ገብቷል "እኔም እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ከእናነተ ጋር ነኝ" ብሏል (ማቴዎስ 28፡20) ይህ ብቻ በቤተክርስቲያን አምልኮ ላይ እንድንገኝ ሊያደርገን ይችላል ምክን ያቱም ጌታ በዚያ እንደሚገኝ ተናግሮአል፡፡ ጠቅላይ ሚንስቴር ቢገኙ መገኘት አንፈልግም ነበር ወይስ አንድ ጠቃሚ ሰው ቢገኙ? እዚህ ግን ጌታ እራሱ ከእኛ ጋር እንደሚገናኝ ሲናገር ይህን አስፈላጊ ቀጠሮ ጠብቀን ልንወድቅ አይገባንም

6. በእያንዳንዱ ስብሰባ ላይ መገኘት እንፈልጋለን ምክንያቱም እኛ እያደረግን ባለው ምሣሌ ቤተሰቦች አሉን የምንወዳቸው ጓደኞች እና በአጠቃላይ የዓለም ህዝቦች እኛን የሚመለከቱን እነሱ እኛን ለመከተል ምሣሌ ለመመሪያም እየፈለጉን ነው ይህን ተረድተን ወደ ትክክለኛው

አቅጣጫ ለመምራት መጣር አለብን፡፡ የነርሱ መዳን እርስዎ ከሚያስቡት በላይ በእኛ ተግባር ላይ የተወሰነ ሊሆን ይችላል ጳውሎስ ለተሰሎንቄ ሰውች ሲፅፍ "ደግሞ እናንተ ቃሉን በብዙ መከራ ከመንፈስ ቅዱስ ደስታ ጋር ተቀብላችው እኛንና ጌታን የምትመስሉ ሆናችው ስለዚህም በመቄዶን ያና በአካይያ ላሉት መዕመናን ሁሉ ምሣሌ ሆናችሁላቸው" (1 ተሰሎንቄ 1፡6~7) ሰዎች እኛ ሲከተሉ ክርስቶስን እንደሚከተሉ ምሣሌ መሆን እንችላለን? አዎን መሆን እንችላለን፡፡ መሆንም አለብን፡፡ በየንዳንዱ ጉባኤ ላይ ለመገኘት አሁኑኑ እቅድ አውጣ በሠዓት ድረስ፡፡ በትክክል ጌታን አምልክ፡፡

7. ለኅብረት እና ለመንፈሳዊ ዕድገት በግል እና በጋራ በጉባኤዎች መገኘት ያስፈልጋል የቤተክርስቲያን አባላት በጭራሽ ካልተሰባሰቡ ቤተክርስቲያን በዚያ በተለየ ማኅበረሰብ ወይም ከተማ ውስጥ እንዴት አንድ ነገር ሊቸምር ይችላል? ያለመሰባሰብ አባላቶች እርስበርሳቸው ሊተዋወቁ አይችሉም፡፡ ጥንካሬያቸውን ማወቅ አይችሉም ሥራቸውን ማቀድ አይችሉም እርስበርሳቸው መረዳዳት እና መበረታታት አይችሉም በሌላ አነጋገር አብዛኛው  የቤተክርስቲያን ሥራ ጥንካሬዋ አፈጻጸሟ ወዘተ የተመካው በጉባኤውላይ ነው፡፡ እንዷ እውነቱ ከሆነ ግን ቤተክርስቲያን ይህንን ከለላት ትሞታለጭ ለዚያም ነው ብቤተክርስቲያኑ ስብሰባ እና  በዬትኛውም ቦታ ሁልጊዜ ባዲስ ኪዳን ውስጥ የምናነበው ለዚህ ነው ጳውሎስና ወንድሞች ሁልጊዜም ከአከባቢው ጉባኤ ጋር ይገናኙ የነበረው፡፡ በስደት ጊዜም እንኳ ቤተክርስቲያኑ አባላት የመገናኘት ዕድሎችን እና መንገዶችን እንዳገኙ ተነግሮናል፡፡ በተመሳሳይም ዛሬም ዘወትር መገናኘታችን አስፈላጊ ነው፡፡ ጌታን ማምለክ እና ሥራውን ማከናወን አለብን፡፡

እናም እነዚህ በጉባኤው ላይ እንድንገኝ ከሚያደርጉን ምክን ያቶች ጥቂቶቹ ናቸው፡፡ ነገር ግን መገኘታችን በወር ወይም አልፎ አልፎ መሄድ እንችላለን ከሚል ሃሳብ ላይ የተመሰረተ መሆን እንደሌለበት ይልቁንስ በየእለት መሄድ አለብን፡፡ የሣምንቱ የመጀመሪያ ቀን ወይም ቤተክርስቲያኑ ለመገናኘት በፈለገቸበት ጊዜ ሁሉ፡፡ ቅሱሳት መጽህፍት "መሰብሰባችንን አንተው" ይላል ይህ የምንገኝባቸውን ሁሉንም ጉባኤዎች ይጨምራል ይላሉ፡፡ በእውነት ለእርሱ ታማኝ እንድንሆን በራሳችን ህይወት ላይ የበለጠ ትኩረት እንድንሰጥ ጌታ ይርዳን፡፡ በቤተክርስቲያን ጉባኤዎች ላይ መገኘት በዚህ መንገድ ለርሱ ታማኝ ከዚያም ታማኝ ሆነንለት እንቀጥላለን፡፡

## ጥያቄዎች

1. በክርስቲያኖች ውስጥ በጣም አሳዛኙ ጉዳይ ምንድነው?

2. ክርስቲያን ጉባኤ ላይ ሳይገኝ ነገር ግን ታማኝ ክርስቲያን ሊሆን ይችላል?
3. የሐይማኖት ድርጅቶች በዓመት ሁለት ጊዜ የሚያመልኩ ምን ይባላሉ?
4. ክርስቲያኖች ከአምልኮ ሲቀሩ የሚያቀርቡትን ሰበብ ጥቀሳቸው
5. ለክርስቲያን ከቤተክርስቲያን ቀርቶ እቤቱ ማምለክ ይቻላል?
6. ትክክለኛ ክርስቲያን ይህን ያደርጋል?
7. መቼ ነው ክርስቲያኖች ከአምልኮ ለመቅረት ሰበብ የሚኖራቸው?
8. ከአምልኮ መከልከል ማለት ምን ማለት እንደሆነ ግለፅ
9. ዕብራዊያን 10፡23~27 አንብብ
10. ለምንድነው ለጌታ ታማኝ መሆን የሚገባን?
11. መሰባሰብን መተው ማለት ምን ማለት ነው?
12. ክርስቲያኖች የአምልኮ ሥርዓቶችን እንዴት ማስታወስ ይችላሉ?
13. ዕብራዊያን 10፡25 የሚነግረን ቀን ዬትኛው ነው?
14. ሆን ብለው ኃጥያት ለሚሠሩ የሚሆነውን ተናገር
15. አምልኮ ላይ የምንገኝበትን ምክንያት ጥቂት ጥቀስ
16. የቀድሞቹ ክርስቲያኖች የሚሰበሰቡበትን ሁለት ምክንያቶች ጥቀስ
17. ትክክለኛው የመሰብሰብ ዓላም ምንድነው?
18. አምልኮ ላይ የማንገኝ ከሆነ ክርስቶስ እንዳዘዘው ልናስታውሰው እንችላለን?
19. የጌታ ቀን መገኘት ካልቻልን ስለ ስጦታ ምን ማድረግ አለብን?
20. ማን ነው እስካዓለም ፊፃሜ ከናንተ ጋር ነኝ ያለው?
21. መቼ ነው ጌታ ከእኛ ጋር የሚሆነው?
22. ከአምልኮ ጋር በተያያዘ ስለአንድ ምሣሌ ተወያዩ
23. በጉባኤያችን ላይ የተመሰረተው ምንድነው?